# የክርክር ዘዴ የተማሪዎችን የመናገር ችሎታ የማጎልበት ሚና በሊሙ ገነት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት


በ

ሙልጌታ ኃ/መስቀል


አማርኛን ቋንቋ በማስተማር ስነ ዘዴ ለድህረ ምረቃ ፕሮግራም ከፊል ማሟያነት የቀረበ ጥናታዊ ጽሁፍ


ጅማ ዩኒቨርሲቲ

የሶሻል ሳይንስና ሂዩማኒቲስ ኮሌጅ

የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ-አማርኛ ትምህርት ክፍል



ነሐሴ 2009 ዓ.ም

ጅማ ዩኒቨርስቲ

# የክርክር ዘዴ የተማሪዎችን የመናገር ችሎታ የማጎልበት ሚና በሊሙ ገነት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት

በ

ሙልጌታ ኃ/መስቀል

አማርኛን ቋንቋ በማስተማር ስነ ዘዴ ለድህረ ምረቃ ፕሮግራም ከፊል ማሟያነት የቀረበ ጥናታዊ ጽሁፍ

ጅማ ዩኒቨርሲቲ
የሶሻል ሳይንስና ሂዩማኒቲስ ኮሌጅ
የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ-አማርኛ ትምህርት ክፍል

ዋና አማካሪ

ማንያለው አባተ(PhD)

ረዳት አማካሪ

አብዱረህማን ፋንታሁን (MA)

ጅማ ዩኒቨርሲቲ
የሶሻል ሳይንስና ሂዩማኒቲስ ኮሌጅ
የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ-አማርኛ ትምህርት ክፍል

ነሐሴ 2009 ዓ.ም

ጅማ ዩኒቨርስቲ

"የክርክር ዘዴ የተማሪዎችን የመናገር ችሎታ የማጎልበት ሚና" በሊሙ ገነት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዘጠነኛ ክፍል ተተኳሪነት " በሚል ርእስ በሙሉጌታ ኃ/መስቀል የትምህርት ማስተር ድግሪ በአማርኛ ቋንቋ ማስተማር ማሟያ የቀረበው ይህ ጥናት በውስጥና በውጭ ፈታኞች ተገምግሞ ተቀባይነትን አግኝቷል፡፡

ፈታኞች

| ስም | ፊርማ | ቀን |
| --- | --- | --- |
| ------------------------ | ------------------- | ------------------------ |
| አማካሪ | | |
| ------------------------ | -------------------- | ------------------------- |
| የውጭ ፈታኝ | | |
| ------------------------ | ---------------------- | ------------------------------- |
| የውስጥ ፈታኝ | | |

# ምስጋና

በመጀመሪያ የረዳኝን እግዝአብሔርን አመሰግናለው፡፡ በመቀጠል ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይሉ የጥናቱን ጽሁፍ በማንበብ ማስተካከያዎችንና ገንቢ ሐሳቦችን በመስጠት ድጋፍ ላደረጉልኝ ለዋና አማካሪዬ ዶ/ር ማንያለው አባተ ከልብ የሆነ ምስጋናዬን አቀርባለው፡፡ የዚህ ጥናት ጽሁፍን በማንበብ ሐሳብ ለሰጡኝ ረዳት አማካሪዬ አቶ አብዱረህማን ፋንታሁንን አመሰግናለሁ፡፡ በመቀጠል የዚህን ጥናት ጽሁፍ በማንበብና ማስተካከያ ሐሳብ በመስጠት ድጋፍ ላደረጉልኝ ለዶ/ር አቢይ አሰፋ እና አቶ መሐመድ ጀማልን  እንዲሁም ስማቸውን ሳልጠቅስ ላለፍኩት ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍል መምህራን  ከልብ አመሰግናለው፡፡ በመጨረሻም ጽሁፉን በመተየብ ለረዳችኝ ወ/ሮ መአዛሽ ታደሰ እና ከጎኔ በመሆን ላበረቱኝ ጓደኞቼ ዘላለም መለሰ፣ ሰለሞን ጎንፋና መገርሳ ጋሹ እንዲሁም በገንዘብ ድጋፍ ላደረገልኝ ጅማ ዩኒቨርሲቲን ከልብ አመሰግናለሁ፡፡

## ማውጫ


**ርዕስ** **ገፅ**

**ምስጋና**……………………………………………………………………………I

**የሠንጠረዥ ማውጫ**……………………………………………………………IV

**አጠቃሎ**……………………………………………………………………………V

**ምዕራፍ አንድ**…………………………………………………………………1

*መግቢያ*……………………………………………………………………………1

1.1. የጥናቱ ዳራ ……………………………………………………………1

1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክኒያት ……………………………………………3

1.3. የጥናቱ መሪ ጥያቄ ……………………………………………………3

1.4. የጥናቱ ዓላማ ……………………………………………………………4

1.5. የጥናቱ መላት……………………………………………………………4

1.6 የጥናቱ ጠቀሜታ …………………………………………………………4.

1.7 የጥናቱ ወሰን ……………………………………………………………5

1.8 የቁልፍ ቃላት ፍች………………………………………………………5

**ምዕራፍ ሁለት**…………………………………………………………………6

ክለሳ ድርሳናትና ተዛማጅ ፅሁፍ …………………………………………6

2.1. ንድፈ ሀሳባዊ ቅኝት ……………………………………………………6

2.1.1. የመናገር ክሂል ምንነት ……………………………………………6

2.1.2. የመናገር ክሂል አላባዊያን …………………………………………7

2.1.2.1 መናገርን የማስተማሪያ መርሆዎች ………………………………9

2.1.2.2 መናገርን በማስተማር የመምህሩ ሚና……………………………10

2.1.2.3 መናገርን ማስተማርያ ስልቶች…………………………………11

2.1.2.4 ውጤታማ የመናገር ክንውኖች ባህሪ……………………………13

2.1.2.5 የመናገር ክሂሊ ምዘና (Assessment of speaking skill)……………13

2.1.3 የክርክር ምንነት ……………………………………………………17

2.1.3.1 በክርክር የንግግር ክሂልን ማስተማር አስፈላጊነት………………19

2.1.3.2 የክርክር ንድፎች……………………………………………………20
2.1.3.3 ቀላል የክርክር ንድፍ………………………………………………….20
2.1.3.4 የክርክር ክፍሎች /The parts of Debate/ ……………………..………21
2.1.3.5 የክርክራዊ ዘዴ ቅድመ ተከተል………………………………………......22
2.1.3.6 የክርክራዊ ዘዴ ትምህርት ዓላማዎችና ጠቀሜታቸው…………………24
2.2 ተዛማጅ ጽሑፍ ቅኝት...……………………………………………………25
ምዕራፍ ሦስት ……………………………………………………………....29
የአጠናን ዘዴ ትንተና……..…………………………………………………29
3.1. የጥናቱ ተሳታፊ ተማሪዎች ……………………..……………………29
3.2 .የሙከራዊ ቡድኑ የክፍል ውስጥ ክንውን ናሙና……………………………..31
3.3. የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ……………………….………………31
3.3.1 ፈተና …………………...…………...……………..………………..31
3.3.2 ምልከታ…………...………………...……………………………..33
3.3. የመረጃ መተንተኛ ዘዴ…………………………………………..…………..36
ምዕራፍ አራት…………………………………………………..……….…38
4.1 የመረጃ ትንተና እና ውጤት ገለጻ…………………………………………38
4.1.1 የውጤት ትንተና………………………………………………………….38
4.1.2 የክፍል ውስጥ ምልከታ መረጃዎች ትንተና………………………………38
4.1.3 የፈተና ውጤት ትንተና…………………………………………………42
ምዕራፍ አምስት…………………………………………..……………………..54
5.1 ማጠቃለያ ፣ መደምደሚያና የመፍትሔ ሀሳቦች……………………………54
5.2 ማጠቃለያ ………………………………………………………………54
5.3 መደምደሚያ……………………………………………………………..57
5.4 የመፍትሔ ሃሳብ…………………………………………………………58
ዋቢ መፅሐፍት ……………………………………………………………..60
አባሪ…………………………………………………………………………..61

# የሠንጠረዥ ማውጫ

ሠንጠረዥ፡2.1 የመናገር ክሂል ቃላዊ ፈተና ትንተና መግለጫ (መመሪያ) ቃላት፣ስዋስው ፣ ንበት እና ፍሰት Brown,(2004:173)……………………………………...17

ሠንጠረዥ 3.1 የምልከታ ቼክ ሊስት…………………………………………………………..39

ሠንጥረዥ 4.1 የመጀመሪያ ዙር የምልከታ ውጤት……………………………………….40

ሠንጠረዥ 4.2 ሁለተኛ ዙር የምልከታ ውጤት…………………………………………42

ሠንጠረዥ 4.3 የሙከራ ቡድን ቃላዊ የመናገር ክሂል ቅድመ ችሎታ ፈተና ውጤት…43

ሠንጠረዥ 4.4 የጥብቅ ቡድን ቃላዊ የመናገር ክሂል ቅድመ ችሎታ ፈተና ውጤት……44

ሠንጠረዥ 4.5 ቃላዊ የመናገር ክሂል የቅድመ ችሎታ ፈተና አማካይ ውጤት…………46

ሠንጠረዥ 4.6. ቃላዊ የመናገር ክሂል ምዘና የቅድመ ፈተና የቲ–ቴስት ስሌት ውጤት..47

ሰንጠረዥ 4.7. የጥብቅ ቡድን የመናገር ክሂል ምዘና ድህረ ፈተና ውጤት………………48

ሰንጠረዥ 4.8. የሙከራ ቡድን ቃላዊ የመናገር ክሂል ድህረ ፈተና ውጤት……………..49

ሰንጠረዥ 4.9. የጥብቅ ቡድኑ እና የሙከራ ቡድኑ ቃላዊ የመናገር ክሂል ምዘና የድህረ ፈተና አማካይ ውጤት……………………………………………………51

ሰንጠረዥ 4.10. የሙከራ ቡድኑ እና የጥብቅ ቡድኑ ቃላዊ የመናገር ክሂል መመዘኛ የድህረ ችሎታ ፈተና የቲ-ቴስት ውጤት……………………………….51

## አጠቃሎ

የጥናቱ ዋና ዓላማ የክርክር ዘዴ የተማሪዎችን የመናገር ችሎታ የማጎልበት ሚና ማየት ነው፡፡ ጥናቱም ፍትነታዊ ስልትን የተከተለ ነው፡፡ መጠናዊና አይነታዊ ዘዴን በመከተል መረጃዎች ተተንትነዋል፡፡ የጥናቱ ተሳታፊዎች በጅማ ዞን በሊሙ ኮሣ ወረዳ በሊሙ ገነት ከተማ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የ2009 ዓ.ም የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ናቸው፡፡ እነዚህም በሁለት ቡድን ማለትም የጥብቅ ቡድን እና የሙከራ ቡድን በመባል ተከፍለዋል፡፡ ጥብቅ ቡድኑ በመደበኛ ወይም በተለምዶአዊ የማስተማር ዘዴ የመናገር ክሂልን ሲማሩ የሙከራ ቡድኑ በክርክራዊ ዘዴ የመናገር ክሂልን የተማሩ ናቸው፡፡ የመረጃ መሰበሰቢያ ዘዴ ሆኖ ያገለገለው በዋናነት ፈተና ሲሆን፣ ምልከታ ተማሪዎች ያሉበትን ደረጃ እንዲገልጽ ጥቅም ላይ ውሏል፡፡ ፈተናው በቅድመ ፈተና እና ድህረ ፈተና የተከፈለ ነው፡፡ በዚህ መሠረት የተማሪዎችን የመናገር ክሂል መመዘኛ በሆኑት ቃላት፣ ሰዋስው፣ ንበት እና ፍሰት ከቅድመ ፈተና ውጤት በመነሳት ያሉበትን ደረጃ በማየት በክርክር ዘዴና በተለምዶአዊ (መደበኛ) የማስተማር ዘዴ ተምረው ያመጡት ውጤት በቃላዊ የመናገር ፈተና ምዘና መለየት ተችሏል፡፡ በዚሁ መሠረት የጥብቅ ቡድኑ በድህረ ፈተና ያገኙት ውጤት ከቅድመ ፈተናው ውጤት ጋር ተመሳሳይ ሲሆን በክርክር ዘዴ የተማሩት ቡድን በሊከርት መመዘኛ ደረጃ (likert scale) ስሌት መሠረት ከበቂ ደረጃ ወደ በጣም ጥሩ ደረጃ ላይ መድረሳቸውን ከጥናቱ በተገኘው ውጤት ማወቅ ተችሏል፡፡ በመጨረሻም የቋንቋ መምህራን በክፍል ውስጥ በክርክራዊ ዘዴ ቢያስተምሩ የተማሪዎችን የመናገር ክሂላቸውን ሊያዳብርላቸው እንደሚችል ተጠቁሟል፡፡

# ምዕራፍ አንድ

# መግቢያ

## 1.1. የጥናቱ ዳራ

ቋንቋ ረቂቅ በሆነ መንገድ ሰዎችን የሚያግባባ፣ በዘፈቀደ የተፈጠረና የሰው ልጆች ብቻ የሚጠቀሙበት ዓይነተኛ መሳሪያ ነው፡፡ ከዚህም የተነሳ ከአራቱ የቋንቋ ክሂሎች ማለትም የመናገር፣ ማዳመጥ፣ ማንበብና መፃፍ ሲሆን የመናገር ክሂል ትልቁን ስፍራ ይይዛል፡፡

ሰው ሀሳቡን፣ አስተያየቱንና ፍልጎቱን ለመግለፅ ማህበራዊ ትስስሮችና ወዳጅነትን ለመፍጠር ንግግርን እንደ መሣሪያ ይጠቀማል በማለት Venkantes warn.S. (1997፡82) ሲገልጽ፣ Ur (1991፡120) ከአራቱ የክሂል ዘርፎች ንግግር ግንባር ቀደምትነት አለው ይላሉ፡፡ ይህም ማለት አንድ ሰው አንድን ቋንቋ ያውቃል ሲባል ቋንቋውን መናገር ይችላል እንደማለት ነው፡፡ ይህም ሌሎች ክሂሎች በንግግር ጥላ ስር ሊታቀፉ እንደሚችሉ ያመለክታል፡፡

በመሆኑም ሰዎች ቋንቋን በመጠቀም በንግግር ለአድማጭ መልዕክት ያስተላልፋሉ፤ ለተላለፉትም መልዕክት ፈጣን ምላሽ ማግኘት ይሻሉ፡፡ በዚህም መሠረት ንግግር የሚቀርብበትን ዓላማ ማሳካት እንዲቻል በተለይም በመማሪያ ክፍል ውስጥ ንግግር ለማድረግ የሚያስችሉ ዘዴዎች ማስተማር እንደሚያስፈልግ Glenn (2003 ፡ 30) ይገልጻሉ፡፡

‹‹… የመናገር ክሂል ትምህርት ተገቢ ዝርዝር ዓላማዎች ተነድፈውለት ጠቃሚ ይዘቶች ተመርጠውለት በልዩ ልዩ የማስተማሪያ ዘዴዎች ልናዳብር ይገባል፡፡›› በማለት የመናገር ክሂል በዘፈቀደ ሳይሆን በትምህርት ማዳበር ወይም ማጎልበት የሚገባ ስለመሆኑ ሰለሞን ሐላፎም (1994፡21) ግራንትን (1987) ጠቅሶ ያስገነዝባል፡፡

ተማሪዎችን በክፍል ውስጥም ሆነ ከክፍል ውጭ ራሳቸውን እንዲያደፋፍሩ በማነሳሳት እንዲናገሩና ሀሳባቸውን እንዲገልጹ ማበረታታትና ማነሳሳት አስፈላጊ ነው፡፡ በመማሪያ ክፍል ውስጥ እና ከመማሪያ ክፍል ውጭ የተማሪዎች የመናገር ክሂል በዝቅተኛ ደረጃ ላይ የሚገኝና ከመሰረቱ ችግር ያለበት መሆኑን በድሉ (1996፡59) ሲያብራሩ በተማሪዎች ላይ

አይን አፋርነትና በራስ ያለመተማመን ሁኔታ መታየቱ የጎላ አድርጎታል በማለት በተግባቦት ሂደት መልዕክት በምክንያትና በውጤት አቀናጅቶ ያለመቅረብና የቋንቋን ስርዓት ያለመጠበቅ ችግር ሲያጋጥማቸው ይታያል ብለው ገልጸውታል፡፡

ይህን መሰል ችግር ለማስወገድ ደረጃቸውን የጠበቁ የመናገር ክሂል ማስተማሪያ ስልቶችን በመምህሩ ተዘጋጅተው በተግባር ላይ መዋል አለባቸው፡፡ ይህ እስካልሆነ ድረስ ግን ከቋንቋ ግቦች አንደኛውን የመናገር ችሎታ ለማዳበር ያስቸግራል፡፡ ስለዚህ የተለያዩ አውዶችን በመፍጠር ተማሪዎች የመናገር ክሂላቸውን ለማጎልበት እንዲችሉ ሁኔታዎችን ማመቻቸት ወሳኝ ነገር መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡

በመሆኑም ይህን ወሳኝ እና አስፈላጊ የሆነውን የመናገር ክሂል ለተማሪዎቻችን ለማስተማር እጅግ ብዙ የሆኑ የማስተማሪያ ስልቶች እንዳሉት ሁሉ፤ ለተማሪዎች የሚቀርበው የማስተማሪያ ስልት ግን በጣም ሳቢና ማራኪ መሆን ይኖርበታል፡፡

የመናገር ክሂል ማስተማሪያ ስልቶች የተለያዩ ቢሆኑም፤ ከእነዚህም አንዱ ክርክር ነው፡፡ እንደ Maryadi አገላለጽ ክርክር ተግባቦትን ለማሻሻል፣ የአስተሳሰብ አድማስን ለማስፋት፣ በራስ መተማመን መንፈስን ለማበልጸግና ንቁ ተሳታፊ የሚያደርግ እና የተለያየ የቡድን አደረጃጀቶችን በማዋቀር ሀሳባቸውን እንዲሰነዝሩ የሚያደርግ እና እውቀታቸውን እንዲለዋወጡ የሚረዳቸው ስነ ትምህርታዊ ይዘት እንደሆነ Maryadi (2008;14-16) ይገልጻል፡፡

በመሆኑም መናገርን በክርክር ዘዴ በማስተማር የተማሪዎችን የመናገር ክሂል መሻሻል ውጤታማነትን ለመፈተሽ ጥናቱ ተካሂዷል፡፡

በዚህ መሠረት ይህ ጥናት በጅማ ዞን በሊሙ ኮሳ ወረዳ ሊሙ ገነት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የ9ኛ ክፍል ተማሪዎችን ተተኳሪ በማድረግ አማርኛ ቋንቋ ትምህርት የክርክር ዘዴ የተማሪዎችን የመናገር ችሎታ የማጎልበት ሚና ፈትሿል፡፡

## 1.2. የጥናቱ መነሻ ችግር

የዚህ ጥናት ርእሰ ጉዳይ የክርክር ዘዴ የተማሪዎችን የመናገር ችሎታ የማጎልበት ሚና የሚል ነው፡፡የዚህ ጥናት ተመራማሪ በተጠቀሰው ርእሰ ጉዳይ ለማጥናት ያነሳሳው ምክንያት ለረጅም ጊዜ በመምህርነት በቆየባቸው ጊዚያት በመማር ማስተማር ሂደት ውስጥ እንዳስተዋለው በክፍል ውስጥ ከግማሽ በላይ የሚሆኑ ተማሪዎች በተለያዩ ርእሰ ጉዳይ ላይ ንግግር ማድርግ፣ ራሳቸውን ማስተዋወቅ እንዲሁም ሀሳባቸውን መግለጽ የማይችሉ መሆናቸውን ተገንዝቧል፡፡ ታዲያ ይህን የመናገር ክሂል በተማሪው ዘንድ ለማዳበር ምን ዓይነት ስልት መጠቀምና ማስተማር አለብኝ? የሚለው አጥኚውን ሲያሳስበው የነበረ ጥያቄ በመሆኑ ለጥናቱ መነሻ ምክንያት ሁኗዋል፡፡ በዚህ ጥናት በክርክር ስልት ትግበራ የተማሪዎችን የመናገር ክሂል እንዴት ማሻሻል እንደሚቻል መርምሯል፡፡

እነ Maryadi (2008;16) Bambang (2006;125) krieger (2005;1) Shan (2005,p.21) ክርክር በቋንቋ የመናገር ክሂል ማስተማር ዘርፍ አይነተኛ ጠቀሜታ እንዳለው ይገልጻሉ፡፡ ይሁን እንጅ አጥኚው በሚያስተምርበት ትምህርት ቤት በክፍል ውስጥ የመናገር ክሂልን ለማዳበር በክርክራዊ ዘዴ ሲማሩ አላየም፡፡

በመሆኑም የክርክር ስልት ትግበራ የተማሪዎችን የመናገር ክሂል እንዴት ያሻሻላል? የክርክር ዘዴን መጠቀም እስከምን ድረስ የመናገር ክሂልን ሊያሻሽል ይችላል? የሚሉት ጉዳዩችን አጥኚው ለማየት ሞክሯል፡፡ ጥናቱም ስኬታማ ከሆነ በክርክር ስልት የመናገር ክሂልን ማስተማር ለስኬታማ የቋንቋ ትምህርት ግብ ይሆናል ብሎ አጥኚው ይገምታል፡፡

## 1.3 የጥናቱ መሪ ጥያቄ

ይህ ጥናት የሚከተለውን መሪ ጥያቄ ይመልሳል ተብሎ ይታሰባል፡፡

- በክርክራዊ ዘዴ ትምህርት አተገባበር የተማሪዎች የመናገር ችሎታ እንዴት ማሳደግ ወይም ማዳበር ይችላል?

## 1.4 የጥናቱ ዓላማ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ የክርክር ዘዴ የተማሪዎችን የመናገር ችሎታ የማጎልበት ሚና በሊሙገነት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት 9ኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት መፈተሽ ነው፡፡በውስጡም የሚከተሉትን ዝርዝር አላማዎችን አንግቧል፡፡

### ዝርዝር ዓላማ

- በክርክር ዘዴ አተገባበር የተማሪዎች የመናገር ችሎታ ውጤታማነትን ተንትኖ ማሳየት፡፡
- ከክርክራዊ ዘዴ ትምህርት ትግበራ በኋላ የተማሪዎች የመናገር ችሎታ መሻሻሉን መመዘን፡፡

## 1.6. የጥናቱ ጠቀሜታ

ይህ ጥናት የሚከተሉት ጠቀሜታዎች ይኖሩታል፡-

1. በክርክራዊ ዘዴ ትምህርት ተጠቅሞ የመናገርን ክሂል ማስተማር የተማሪዎችን የመናገር አቅም ሊያሳድግ ይችላል፡፡

2. መምህራን በመማር ማስተማር ሂደት ውስጥ የመናገር ክሂልን ለማስተማር ክርክራዊ ዘዴን እንዲጠቀሙ ያስችላቸዋል፡፡

3. ወደፊት ከዚህ ጥናት ጋር ተያያዥነት ያለው ጥናት ለማካሄድ ለሚፈልጉ ተመራማሪዎች እንደመነሻ ሆኖ ሊያገለግል ይችላል ፡፡

## 1.7 የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናት የክርክር ዘዴ የተማሪዎችን የመናገር ችሎታ የማጎልበት ሚና በሚል ርእስ የተጠና ነው፡፡ጥናቱ በሊሙ ኮሳ ወረዳ በሊሙ ገነት ከተማ በሊሙ ገነት  ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በ2009 ዓ.ም ዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎችን ብቻ ተተኳሪ በማደረግ ነው፡፡ መናገርን ለማስተማር እንደ መሳሪያ የተጠቀመው ክርክራዊ ዘዴን ብቻ እንጂ ሌሎች ማስተማሪያ ዘዴዎችን አልተጠቀመም፡፡በዚህም ክርክራዊ ዘዴ በቋንቋ ትምህርት ውስጥ መናገርን ለማስትማር ያለውን ሚና መርምሯል፡፡ሌሎች ክሂሎች ላይ ሊደርስ የሚችለውን ተጽእኖ ትኩረት አላደረገም፡፡ስለሆነም በተጠቀሱት ነጥቦችና ምክንያቶች ጥናቱን ውስን አድርገውታል፡፡

# ምዕራፍ ሁለት

# የተዛማጅ ድርሳናት ክለሳ

## 2.1 ንድፈ ሀሳባዊ ቅኝት

### 2.1.1 የመናገር ክሂል ምንነት

እንደ scoot ,(2005;79) አገላለጽ “ንግግር በአንደበት ክፍሎች በተቀናጀ የድምፅ አፈጣጠር ስረዓት አማካኝነት የሚፈጠር አፍላቂ ክሂል ነው፤ንግግር አእምሮአዊ ችሎታን የሚጠይቅ የአስተሳሰብ እውቀት በጨመረ ቁጥር እያደገ የሚሄድና በበቂ ልምምድ ውስጥ የሚዳብር ነው፡፡” በማለት ይገልጻሉ፡፡ እንደገናም ንግግር የሰው ልጅ ፍላጎቱን ስሜቱን አጠቃላይ ሀሳቡን ወይም አመለካከቱን ለሌላ ሁለተኛ ወገን ለመግለፅ የሚጠቀምበት ሂደት ነው በማለት Venkantes warn.S.(1997፡83) ያብራራሉ፡፡በማያያዝም warn.S. እንደሚሉት ቋንቋ የሚባል ነገር ሲነሳ ንግግር ቀዳሚውን ስፍራ ይይዛል ይላሉ፡፡እንዲሁም ሰው ሀሳቡን አስታየቱን ፍላጎቱን በመግለፅና ማህበራዊ ትስስሮችንና ወዳጅነትን ለመፍጠር ንግግርን እንደ መሣሪያ ይጠቀማል በማለት ይገልጻሉ፡፡

Ur, (1991፡ 120) ከአራቱ የክሂል ዘርፎች ንግግር ግንባር ቀደምትነት አለው ይላሉ፡፡ አንድ ሰው አንድን ቋንቋ ያውቃል ሲባል ቋንቋውን መናገር ይችላል ማለት ነው፡፡ አንድን ቋንቋ በልምድ ወይም በመማር የሚናገር ሰው የቋንቋውን የድምፅ ምዕላድ፣ የቃላትና የሰዋሰው ስርዓት ጠብቆ መናገር ይጠበቅበታል፡፡ በንግግር ትምህርት ውስጥ ተማሪዎች ከነዚህ የቋንቋ ንጥረ ነገሮች በተጨማሪ የተናጋሪው ህብረተሰብ ባህል፣ ስነልቦና፣ አመለካከትና ማህበራዊ እሴቶች በመግባባቱ ሂደት ከፍተኛ ፋይዳ እንዳላቸው መገንዘብ ያሻል፡፡ የመናገር ትምህርት ከነዚህ ተጨባጭ ጉዳዩች ጋር በተገናዘበ መልኩ የመናገር ክሂል ኖሮአቸው መጠቀም እንዲችሉ መርዳት ነው፡፡

ከቋንቋ ክሂሎች ውስጥ አንዱ የሆነው የመናገር ክሂል በጣም አስፈላጊ እና ተማሪዎች እርስ በርሳቸው ጥሩ ግንኙነት ሊያደርጉ የሚችሉበት እንዲሁም ከሌሎች ጋር የምንገናኝበት ቃላዊ የቋንቋ መሣሪያ ነው በማለት Fulcher (2003:28) ያብራራሉ፡፡

በአጠቃላይ ንግግር አንድን ነገር ተረድተን የምንቀበለው እንዲሁም ምላሽ በመስጥት በማህበራዊ ሂደት ውስጥ የምንግባባበት መሳሪያ ነው፡፡ ንግግር አንድን ነገር ለመግለጽ ድምጽንና ቃላትን በማውጣት ቋንቋን በገሃዱ አለም ውስጥ መጠቀም መቻላችን ነው፡፡በአጭሩ ንግግር ስሜትን በቃላት፣በሀረጋትና በአረፍተ ነገር በመጠቀም ከሌሎች ጋር የምንግባባበት ትርጉም ያለው የእርስ በርስ ግንኙነት ማድረግ ነው፡፡

## 2.1.2 የመናገር ክሂል አላባውያን

Harmer (2003:269) እንደሚያስረዱት የመናገር ችሎታን ለማዳበር የሚከተሉት መሰረታዊ ነገሮች አስፈላጊ ናቸው ይላሉ፡፡

### 1. የቋንቋ ገፅታ

ይህም የሚከተሉትን ንኡሳን መሰረታዊ ጉዳዮችን ይመለከታል፡፡

ሀ. ተያያዥ ንግግር፡- ስኬታማ ተናጋሪዎች ፍሰትን የጠበቁ ንግግሮችን ይጠቀማሉ፡፡ በተያያዥ ንግግር ድምጾች ይታደሳሉ፣ ይወገዳሉ፣ ይጨመራሉ ወይም ይደክማሉ፡፡ በዚህም ምክንያት ተማሪዎች ተያያዥ ንግግራቸውን እንዲያሻሽሉ ወደነዚህ ክንውኖች ልናስገባቸው ይገባል፡፡

ለ. የግልጸት ግብአት፡- አፈ ፊት የአንድን ንግግር ቅላጼን መጥበቅና የመላላት ለውጥን ከድምጹ ከፍታና ፍጥነት በተጨማሪ ሌሎች አካላዊና ቃላዊ ያልሆኑ ምልክቶችን በመጠቀም ስሜቱን ሊገልጽ ይችላል፡፡ እነዚህን ግብአቶችን መጠቀም ፍችን እንዲጎናጸፍ ያስችሉታል፡፡ ምክንያቱም ስሜቱን በተጨማሪ አገላለጾች እንዲገልጽ ያስችሉታል፡፡ ተማሪዎችም ስኬታማ ተግባቢ ለመሆን እነዚህን ቅንጣት የቋንቋ ገጽታዎችን ሊለማመዱ ይገባል፡፡ የታላሚውን ቋንቋ ድምፅን በማስረዘምና በመጫን (በማሳጠር) እንደየ ባህሪያቱ እየለዋወጡ ሊናገሩት ይችላሉ፡፡

ሐ. ቃላትና ሰዋሰው፡- ቅጥልጣይ ንግግሮች ማቆሚያቸው የተለያዩ ቋሚ ቃላትን በመጠቀም ነው፡፡ በተለይም በቋንቋው አገልግሎታዊ ብቃት ላይ ሲሆን የሐሳብ ማሰሪያ ቃላት ጥቅም ላይ ይውላሉ፡፡

መምህራኖችም የተለያዩ የሐሳብ ማሰሪያ ቃላትና ሐረጋትን በመምረጥ ያቀርባሉ፡፡ ከእነዚህም ሰላምታ መስጠትና መቀበል፣ መስማማትንና ያለመስማማትን የሚገልጹ ቃላትና ሐረጋት ለአብነት ያህል ይጠቅሳሉ፡፡

መ. የስምምነት ቋንቋ:- ስምምነትን ለመፍጠር የምንጠቀምበት የቋንቋ ሁኔታ ግልፅና መዋቅሩ የተስተካከለ ውጤታማ ንግግር ማድረግ አለብን፡፡ አንድን ሰው ስናዳምጥ ግልፅ የሆነ ንግግርን መስማት እንፈልጋለን ይህ ደግሞ ለተማሪዎች ዋነኛው ጉዳይ ነው፡፡

በአጠቃላይ ንግግር የቃላት ጋጋታና የሰዋስው ሥርአታዊ አወቃቀር ማወቅ ብቻ ሳይሆን ከላይ የተጠቀሱትን አላባዎችን የመካን ነው፡፡ ምክንያቱም እነዚህን አላባዎች ከተካንን በሁሉም ተግባቢዎቻችን ዘንድ ተቀባይነትን እናገኛለን፡፡

### 4. አዕምሮአዊ ወይም ማህበራዊ ሂደት

የተናጋሪው የመናገር ክሂል ውጤታማነት በፈጣን የመናገር ክህሎት ሂደት ላይ የሚመሠረት ነው በማለት Harmer (2003; 269-270) ያስረዳሉ፡፡ ይህም የሚከተሉትን መሰረታዊ ነጥቦች ተፈጻሚ ማድረግ ነው፡፡

ሀ. የቋንቋ ሂደት :- የቋንቋ ሂደት ቃላት ስርአት ጠብቀው በተቀናጀ አግባባዊ መልክ ትርጉምን ይዘው የሚተላለፍ ሂደት ነው፡፡

ለ. ከሌሎች ጋር ማዋሃድ :-ውጤታማ ንግግር ጥሩ የማዳመጥ ችሎታን ይጠይቃል፡፡ የሌሎችን ተሳታፊዎች ስሜት አረዳድ መገንዘብ፣ እንዲሁም ስነልሳናዊ እውቀት ምላሽ መውሰድ ወይም ሌሎች የሚያደርጉትን መፍቀድ፡፡

ሐ. የመረጃ ልውውጥ ሂደት:- የአድማጫችን ስሜቶች ወይም ሀሳቦች የምንሰጠውን ምላሽ በዚያው ጊዜን አብሰልስለን መመለስ ይጠበቅብናል፡፡

መ. መናገርን ማሰተማር :- የመናገር ችሎታ የሚያዳብረው ከሌሎች ጋር ንግግር ወይም ምልልስ ስናደርግ ነው፡፡ በመሆኑም አብዛኛው የቋንቋ ተማሪዎች ንግግርን የቋንቋ ችሎታ በእጅጉ ጠቃሚ አድርገው ያስቡታል፡፡ እድገታቸውን የንግግር ተግባት ሂደትን በመጨረስ ይገመግሙታል፡

ይህንን የመናር ክሂል አእምሯዊ ሂደት ትስስርን በተመለከተ Harmer (2003:269) በተጨማሪ ሲያብራሩ፡-

> *ንግግር በተናጋሪውና በአድማጭ መካከል የሚከናወን የሁለትዮሽ ሂደት ነው፡፡ የማፍለቅ ክሂል (productive skill) የሆነው የመናገር ክሂል ይዳብር ዘንድ የመቀበል (receptive skill) ክሂል የሆነውን የማዳመጥ ክሂልን መዳበር አለበት፡፡ የሁለቱ ክሂሎች መዳበር በእጅጉ የተቆራኘ ነው፡፡ በአብዛኛው የቋንቋ ትምህርት የክፍል ውስጥ ተግባራት በተለይ አንድ የቋንቋ ክሂል ላይ ማተኮር አስፈላጊ ይሆናል፡፡ለምሳሌ ለአንድ ክፍለ ጊዜ የታዘዘው የትምህርት አላማ ማዳመጥ ወይም መናገር ማስተማር የሚል ይሆናል፡፡ ይሁን እንጂ በዚህ ዓይነት ሁኔታ ቢሆንም በአራቱ የቋንቋ ክሂሎች መካከል ሊኖር የሚችለውን ትስስር መዘንጋት የለብንም፡፡ በተለይ ንግግር በተናጋሪና በአድማጭ መካከል የሚካሄድ የሁለትዮሽ ቃላዊ ተግባቦት ነው፡፡ ይህም ማለት ንግግር የአድማጭን ምላሽ የሚፈልግ ክሂል ነው፡፡*

ከዚህ መረዳት የሚቻለው የመናገር ክሂል ብቻውን የሚበለጽግ ክሂል ብቻ ሳይሆን ከማዳመጥ ክሂል ጋር የሚበለጽግ መሆኑን ነው፡፡ በመሆኑም የመናገር ክሂል የአድማጭን ትኩረት የሚፈልግ በመሆኑ ከማደመጥ ጋር ያለው ትስስር ከፍተኛ ነው፡፡

2.1.2.1 መናገርን የማስተማሪያ መርሆዎች፡-

Nunan (2003:54-56) መናገርን ለማስተማር የተወሰኑ መመሪያዎች አሉ በማለት እንደሚከተለው ይዘረዝራቸዋል፡-

1. በሁለተኛ ቋንቋ እና በመጀመሪያ ቋንቋ መካከል ያለውን የልዩነት አውዳዊ የእውቀት ትምህርት መኖሩን ማሰብ፤ ምክንያቱም ማህበረሰቡ በብዛት የሚጠቀመው በየትኛው የቋንቋ አውድ ነው? በመጀመሪያ ቋንቋ ወይስ በሁለተኛ ቋንቋ እኝህን ለይቶ ማወቅ፡፡
2. ተማሪዎች በሚናገሩት ንግግር ፍሰት ተያኙነት ያለው ሙሉ መእክት ያዘለ መሆን እንዳለበት የንግግር ልምምድ በመስጠት የአንደበት ርቱዕነት እንዲኖራቸው በትክክል ከሚሉት ከታላማዊ ቋንቋ ጋር የሚዛመድ ሲሆን እንዲሁም የንግግር ፍሰት(fluency)

የምንለው ተናጋሪው ቋንቋውን ሲጠቀም በፍጥነትና በራስ መተማመን በተከታታይ የሚያፈሰው የቃላትን ፍሰት ይሆናል፡፡

3. መምህሩ የራሱን በመወሰን ተማሪዎች የሚናገሩበትን እድል በማዘጋጀት በቡድን እና በጥንድ እንዲሰሩ ወይም እንዲወያዩ ማድረግ፡፡

4. የፍች ስምምነትን ያካተቱ ተግባራትን የያዘ የመናገር እቅድ መምህሩ ማቀድ አለበት፡፡
5. በንግግር ሽግግርና መስተጋብር ሂደት ውስጥ የሚካተቱት መመሪያዎችና ተግባራትን የያዙ የክፍል ውስጥ ክንውኖችን መምህሩ መንደፍ ይጠበቅበታል፡፡

### 2.1.2.2 ንግግርን በማስተማር የመምህሩ ሚና

የመናገር ክሂልን ለማስተማር እጅግ ብዙ የሆኑ ውጤታማ ሚናዎች መናገርን በማስተማር ሂደት ውስጥ ይገኛሉ በማለት Rubati Richa (2010፡17) እንደሚከተለው ይገልጻል ፡-

1. ታላሚውን ቋንቋ በትምህርቱ ዙርያ ብቻ መጠቀም በቂ አይደለም፡፡ ይህንኑ ታላሚ ቋንቋ በክፍል ውስጥ ተማሪዎች እንዲግባቡበት በማድረግ ተሳትፎአቸውን ማሳደግ፡፡
2. የተለያዩ ጥያቄዎችን ተማሪዎች እንዲመልሱ በጥቂት በማሳየት ተሳትፏቸውን እንድያሳድጉ ማድረግ፡፡
3. ርዕሱን ከተማሪዎቹ ዳራ ጋር እንዲገናኝ ማድረግ፡- ተማሪዎቹ የፈለጉትን ቢሉ ለርዕሱ አስተዋኦ እንዳለው ማሰብ፣
4. ዝምታቸውን በመታገስ፣ በተደጋጋሚ የሚታይባቸውን ችግር ለይቶ ማሳየትና ጸጥታቸውን እንዲሰብሩ ማበረታታት፣
5. ተማሪዎች የሚናገሩትን ዓረፍተ ነገር ደጋግመው እንዲሉት ማበረታታት በቀጣይነትም እንዲጠቀሙበት ማሳየት፡፡
6. ከተማሪዎች ጋር የሚደረገውን ልውውጥ በማርዘም ገለጻን በመጨመር፣ ለተናጋሪዎች ትኩረት በመስጠት ሃሳባቸውን እንዲቋጩ ማድረግ፣
7. ተማሪዎች መናገርን በሚተገብሩበት ጊዜ ግምገማና ውሳኔ ከመስጠት ይልቅ ሰፊ ገለፃ በመስጠት ጥሩ ምጋቤ ምላሽ እንዲያገኙ ማድረግ፡፡

8. በክፍል ውስጥ ተሳትፎ የተማሪዎችን በስም በመጥቀስ ጥሩ እንዲሰሩ በግልፅ መናገር፣ ማበረታታት፡፡

### 2.1.2.3. መናገርን ማስተማርያ ዘዴዎች :-

እንደ Harmer (2003:27) አገላለጽ ለመናገር ማስተማርያነት የሚያገለግሉ ዘዴዎች የመሚከተሉትን ይመስላሉ፡-

**1. ጽሑፎችን መተግበር፡–**

ይህ አይነቱ ትግበራ ተማሪዎች በየትኛው ስፍራ (ቦታ) በሚያደርጓቸው ጭውውቶች ላይ ወይም በመማሪያ መጽሐፋቸው ላይ የሚያገኙትን ገፅ ፅሑፎች በማየት ወደ ፊልምነት በመቀየር እየተገበሩ እንዲጫወቱ ያበረታታቸዋል በማለት ይገልፃሉ፡፡ ተማሪዎች ሁል ጊዜ የኛን ንግግር (ምልልስ) መልሰው እራሳቸው ይሉታል፡፡ይህ አይነቱ ልምምዳቸው በክፍል ውስጥ ወጥተው እንዲናገሩ ያበረታታቸዋል፡፡

**2.ተግባቦታዊ ጭውውት፡–**

ሁል ጊዜ በጭውውት የተመሠረተ የንግግር ትግበራ (እንቅስቃሴ) ተማሪዎች ካለፍራሃት መናገርን እንዲለማመዱ ያደርጋቸዋል፡፡ በጭውውት ላይ የተመሠረተ ትግበራዊ እንቅስቃሴ ተማሪዎች ሀሳባቸውን እንዲገልፁ፣ እንዲተነብዩ ነገሮችን እንዲያቃልሉ እንዲሁም ምግባቤ ምላሽን በመጠየቅ ራሳቸውን እንዲመዝኑ ያደርጋቸዋል፡፡

**5. ውይይት**

ርዕስ ተኮር ወይም ተግባር ተኮር ክንውን ለተማሪዎች በቡድን የመወያያ ምንጭ በመስጠት በጋራ ሀሳባቸውን እንዲያቀርቡ ማድረግ፡፡ የውይይቱ ርዕስ በመምህሩ ቢመራ የሚደገፍ ነው፡፡ ሁሉም ተማሪዎች በዚህ ትግበራ የመናገር እድል ያጋጥማቸዋል፡፡ ለምሳሌ የክፍሉን ተማሪ አንድ ርዕስ መርጦ በዛ ርዕስ ላይ (disagree discussion) እስማማለው አልስማማም በሚል ውይይት በመፍጠር ለምን? እንዴት? እያሉ ጥያቄዎችን በማምጣት እንዲነጋገሩ ማድረግ፡፡

## 6. የመናገር ዝግጅት

ተማሪዎች በሰዎች ዘንድ ሊደመጥ የሚችል ንግግርን በማዘጋጀት በመረጡት ርዕሰ ጉዳይ ላይ ንግግር እንዲያደርጉ ማድረግ፡፡ ተማሪዎቹም ካዘጋጁት የንግግር ጽሑፍ ከማስታወሻቸው ወይም በፅሑፍ መልክ በማድረግ በተማሪዎች ፊት ለፊት ወጥተው እንዲደሰኩሩ ያደርጋል፡፡ የንግግር (presentation) ሲዘጋጅ ጠቃሚ የሆኑ የንግግር ዘውጎችን በጥሩ ሁኔታ በማቀናጀት ለተናጋሪውም ለአድማጩም ሳቢ በሆነ መልክ መቅረብ መቻል አለበት፡፡

## 7. ማስመሰልና ሚናዊ ትወና

ይህ ማስመሰል የምንለው ሚናዊ ትወና ጋር ይመሳሰላል፡፡ ከሚናዊ ትወና የሚለይበት ማስመሰል ሰፋ ብሎ ስለሚዘጋጅና ብዙ ማብራሪያ ስለሚሰጥ ነው፡፡ በምናቡ ያለውን ነገር አስመስሎ በንግግር ማቅረብ ነው፡፡ በማስመሰል ንግግር ውስጥ ተማሪዎች የተለያዩ ነገሮችን ወደ ክፍል በማምጣት እውነታዊ አካባቢን ለመፍጠር ይሞክራሉ፡፡ ሚናዊ ትወና እና ማስመሰል ለተማሪዎች ከፍተኛ ጥቅም አለው፡፡ በራሳቸው መተማመንን ይፈጥራል፡፡ ተማሪዎችን ያነሳሳል፡፡ ለምሳሌ ተማሪዎች እንደ ዘፋኝ መተግበር ሲፈልጉ የተለያዩ የሙዚቃ መሣል የድምፅ ማጉያዎችን በመያዝ ወደ ክፍል ውስጥ ይዞ በመምጣት ያስመስላሉ፡፡ እንዲሁም ለሌላው ተማሪው የሚያበረታታቸው መንገድ ሚናዊ ትወና ነው ይህ ተማሪዎች በተለያዩ ማህበራዊ አውደ ውስጥ የተለየ የራሳቸው ሚናዎች አሏቸው፡፡ በዚህ በሚናዊ ትወና ክንውን ውስጥ መምህሩ ለተማሪው የተለየ መረጃ በመስጠት ተማሪው የሚሰማውን ወይም የሚያስበውን እንዲናገሩ ያደርጋል፡፡ ወደ ተለያዩ ምህበረሰብ አካላትም የላካቸውን መልዕክትም እንዲያስተላልፉ ያደርጋል፡፡ በዚህ አጋጣሚ ተማሪዎች ንግግርን እንዲለማመዱና እንዲተገብሩ ያደርጋቸዋል፡፡

## 8. ክርክር

ክርክር ሁለት ተቃራኒ ሀሳብ ወይም ነጥብ ያለውን አመለካከት ይዞ በመቅረብ የሚከራከሩበትና የሚነጋገሩበት ነው፡፡ ክርክር በሁለት ተቃራኒ ቡድኖች መካከል የሚደረግ በተገኘው አጋጣሚ ተቃራኒ ቡድኑ ይዞ የቀረበውን መረጃ ለመከላከል ወይም ለመርታት የሚያደርግ የመናገር ዓይነት ነው፡፡

እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት የመናገር ልምምድ ትግበራዎች በክፍል ውስጥ እንዲናገሩ ያበረታታቸዋል፡፡ መምህሩም የተማሪዎችን ደረጃ በመለየት የሚስማማቸውን የመናገር ማስተማሪያ ዘዴ በመምረጥ በክፍል ውስጥ ቢጠቀም ይመረጣል፡፡ እያንዳንዱ የመማር ማስተማር ሂደት ተማሪውን በክፍል ውስጥ እያዝናና የሚያስተማር እና እያጫወተ የሚያስተምር መሆን አለበት፡፡ በዚህ መንገድ የሚደረግ የትምህርት አሰጣጥ በቀላሉ ተማሪዎች እውቀትን እንዲገበዩ ያስችላቸዋል፡፡

### 2.1.2.5 ውጤታማ የመናገር ክንውኖች ባህሪ

Ur, (1991፡120) ውጤታማ የመናገር ክንውኖችን እና መናገርን ለማጎልበት የሚያስችሉ ተግብራት በአብዛኛው ተማሪው ላይ የሚያተኩሩ ናቸው፡፡መናገርን ማስተማር በአብዛኛው ተማሪው ላይ የሚያተኩሩ ናቸው ፡፡መናገርን ማስተማር የሚቻለው አስተማሪው እየተናገረ ሳይሆን ሰልጣኙ እየተናገረ መናገርን መማሩ ነው፡፡በማለት ሲገልፁ፤ ውጤታማ የመናገር መልመጃ ባህሪያትን በአራት ነጥቦች ይከፍሏቸዋል፡፡ እነሱም፡-

1. ተማሪዎች ብዙ እንዲናገሩ የሚያበረታታ፡- ለመናገር ክሂል የተመደበውን ክፍለ ጊዜ በተማሪዎች ንግግር ብቻ የሚሸፈን መሆን አለበት፡፡
2. የተማሪዎች የክፍል ተሳትፎን የሚያመለክት:- የክፍል ውይይት በጥቂት ተናጋሪ ተማሪዎች ብቻ መያዝ የለበትም፡፡ ሁሉም ተማሪዎች የመናገር እድል ማግኘት አለባቸው፡፡ በክፍል ውስጥ እኩል ተሳትፎ መስፈን ይኖርበታል፡፡
3. ከፍተኛ ንሸ (መነሳሳትን):– መነሳሳትን የሚፈጥሩ ተማሪዎች የሚተላለፈውን ትምህርት የሚወዱትና ከፍተኛ ጠቀሜታ ያለው ከሆነ ብዙ ለመናገር ፍላጎት ያድርባቸዋል፡፡ በተጨማሪም የአላማው ተካፋይ ለመሆን ብዙ መናገር ይፈልጋሉ፡፡
4. የሚናገሩት ቋንቋ ተቀባይነቱ የጠበቀ ሲሆን:- እርስ በርስ እየተቀባበሉ በመግባባት ተቀባይነቱ ተጨባጭነት ያለው እንዲሁም ትክክለኛነቱ የጠበቀ ቋንቋ መናገርን ይመለከታል፡፡

### 2.1.2.5. የመናገር ክሂል ምዘና (ግምገማ) (Assessment of speaking skills)

የመናገር ክሂል ፈተናን በተመለከተ Wijarwadi (2008;18) ሲገልጹ የመናገር ክሂልን መፈተን ውስብስብ ፣ አሰቸጋሪ እና ጊዜን የሚጠይቅ እንዲሁም በውስጡ የተለያዩ

ክሂልዎችን በማዳበር በአንድ ጊዜ የተለያዩ ችሎታዎችን መመዘን መሆኑ ነው፡፡ይሁን እንጅ ይህ ሲባል ይላሉ የመናገር ክሂልን መፈተን ፈጽሞ የማይቻል ሂደት ነው ማለት ግን አይደለም በማለት ይገልጻሉ፡፡ Rabab'ah (2003,a;67-68) ሲያብራሩ የመናገር ክሂል የሚመዘነው ይላሉ የንግግሩን ጠቅላላ ሀሳብ በመውሰድ መገምገሙ ይበልጥ ተግባራዊ ያደርገዋል ይላሉ፡፡ጨምረውም መምህሩ የተለየ ጊዜ ሰጥቶ የንግግሩን ፍሰት መገምገም የለበትም ፡፡ነገር ግን የተማሪውን የርስበርስ ውህደትና ተሳትፎ በመመልከት የንግግሩን ሂደት መወሰን ይችላል በማለት ይገልጻሉ፡፡

የመናገር ክሂል መመዘኛዎችን Hughes, A. (2003:53-55) በሦስት ይከፍላቸዋል፡፡እነዚህም ቃለ መጠይቅ ፣ ከጓደኛ የሚያደርጉት የርስ በርስ ምልልስ እና የድምጽ ቀረጻ ምላሽ መስጠት ናቸው ይላሉ፡፡በዚህ ጥናት አጥኝው የተጠቀመው የጥያቄዎችን የእርስ በርስ ምልልስ እና ቃለመጠይቅን ነው፡፡ተማሪዎችን እርስ በርስ እንዲነጋገሩ ስናድረግ ተመሪዎች ተመጣጣኝ የሆነ የቋንቋ ክህሎት እንዲኖራቸው ያደርጋል፡፡ምክንያቱም አንዱ በሌላው ላይ ተጽእኖ እንዳያደርግ ይረዳል፡፡Hughes ጨምሮ ሲያበራራ መምህሩ ለተሳካ የመናገር ክሂል ግምገማ ከዚህ በታች ባሉት ነጥቦች ለይ በመመስረት መጠቀም እንደሚችል ያስረዳል፡፡

1. መምህሩ ማሳደግ በፈለገበት የመናገር ክህሎት ፈተና መስጠት ይችላል፣
2. ፈተናው ለተማሪዎችም ሆነ ለሌሎች መምህራን ግልጽ መሆን አለበት፣
3. ፈተናው ግልጽ የሆነ አላማ ይኑረው፣
4. ናሙናውን ያለማጥበብና ውጤቱን ቀድሞ አለመገመት፣
5. ፈተናው በመመዘኛ ነጥቦች ይቀናጅ፣
6. ቀጥተኛ ፈተናን መጠቀም፡፡

በአጠቃላይ Dewi (2010; 2) Syakur 'ን (1987; 3) ጠቅሶ አምስት ዋና ዋና የመናገር ክሂል መመዘኛ ሂደቶችን አስቀምጧል፡፡እነርሱም ንበት ፣ ስዋስው ፣ ቃላት ፣ ፍሰት እና መልመጃዎች ናቸው፡፡ይህንኑ Brown (1997,p-4) አምስቱን የመናገር ክሂሊ መመዘኛ የተባሉትን እንደሚከተለው አብራርቷል፡፡

1. **ንበት**:-ተማሪው በሚናገርበት ጊዜ ያለቨኘርታ ግልጽ በሆነ መልክ ሀሣቡን በትክክልመግለጽ መቻል፡፡ይህም የተማሪውን ስነ-ድምጽ ሂደት ለይቶ የማወቅ ጉዳይ ነው፡፡
2. **ስዋስው**:-በቋንቋው ህግ መሠረት ተማሪው ትክክለኛ ዓረፍተነገር እና ንግግር በመጠቀም ሀሣቡንና ችሎታውን በትክክል እንዲያወጣ ማድረግ፣
3. **ቃላት**:- ያለቃላት ማንም የራሱን ሀሣብ በቃልም ሆነ በጽሑፍ መግለጽ አይችልም፡፡ስለዚህ ተገቢውን ቃላት ማወቅ ጥሩ ተግባቦት እንዲፈጥር ያደርጋል፡፡
4. **ፍሰት:-** ፍሰት ማለት ተማሪው በትክክልና በግልጽ መናገር መቻል፡፡በአንድ ቋንቋ ውስጥ ፍሰት የሚጠበቅ ሲሆን የትክክለኛ ንበት ምልክቶችም ሀሣቦችን ያለችግር ወይም ያለማቆራረጥ መግለጽ መቻል ነው፡፡
5. **መልመጃ**:- አንድን ምንባብ መሠረት በማድረግ ቃላዊ ንግግርን እንዲያወጣ ማነሣሣት፣

በአጠቃላይ ለተሳካ የመናገር ክሂል ግምገማ የመምህሩ ድርሻ ከፍተኛ ነው፡፡ይህም ማለት ለተማሪው የተመቻቸ ሁኔታን በመፍጠር እና ተማሪዎች ያለስጋት የራሳቸውን ሀሣብ እንዲለዋወጡ ሙሉውን እድል መስጠት መቻል ነው፡፡ ይህም የሚሆነው ተማሪውን ማእከል ያደረገ የመማር ማስተማር ሂደት ሲከናወን ነው፡፡ አክሎም Rababah (2003:67-68) የመናገር ፈተና ለተማሪዎች መስጠት አድካሚ እንደሆነ ቢታወቅም፣ ሰፊ ጊዜና ቦታ ሰጥቶ መፈተን ግን ተማሪዎች ያሉበትን ደረጃ ማወቅ ይቻላል በማለት ይገልጻል፡፡

በማያያዝም Brown, (2004:173 ) ሲገልጹ ቃላዊ ንግግርን ለመገምገም የሚከተሉትን የመመዘኛ ነጥቦች በትንተና አስቀምጠዋል፡፡ እነሱም ቃላት፣ ስዋስው ፣ ንበት፣ ፍሰትና መልምጃዎች ናቸው፡፡እነዚህን የመመዘኛ ነጥቦች Brown ሲያብራሩ ለከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎችን በቃላዊ የመናገር ፈተና ለመመዘን ጠቃሚና አግባብ ያላቸው ናቸው በማለት ገልጸዋል፡፡አጥኝው በዚህ ጥናት ተማሪዎችን ቃላዊ የመናገር ክሂል ፈተና ለመፈተን፤ ቃላት፣ ስዋስው ፣ ንበትን እና ፍሰትን ተጠቅሟል፡፡እነዚህን እያንዳንደቸውን ሃያ አምስት ነጥብ በመስጠት ወደ መቶኛ ይለወጣሉ፡፡እኝህ ቃላዊ የመናገርን ፈተና መመዘኛ ነጥቦችም በሚከተለው ሠንጠረዥ ተተንትነው ተቀምጠዋል፡፡

ሠንጠረዥ፡2.1 የመናገር ክሂሊ ቃላዊ ፈተና ትንተና መግለጫ (መመሪያ) ቃላት፣ስዋስው ፣

ንበት እና ፍሰት Brown,(2004:173)

| የ መና ገ ር ክ ሂ ል | ተ.ቁ | ማመላከቻ | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ቃላት | 1 | ተማሪው ሃሳቡንና ስሜቱን ለመግለጽ በቂ ቃላትን ይጠቀማል | | | | | |
| | 2 | ተማሪው ሁኔታዎችንና ሃሳቡን ለመግለጽና ለማስተዋወቅ ተስማሚ ቃላትን ይመርጣል | | | | | |
| | 3 | ተማሪው የአድማጭን ስሜት ወይም መረዳት በመገንዘብ አማራጭ ቃላትን የመጠቀም ችሎታ አለው | | | | | |
| | 4 | ተማሪው በተሰጠው ርእስ ላይ ገለጻ እና ማብራሪያ ለመስጠት በቂ ቃላት አለው | | | | | |
| | 5 | ተማሪው ቃላትን በተገቢው ቦታ ይጠቀማል | | | | | |
| ስ ዋ ስ ው | 1 | ተማሪው ምክንያታዊ በመሆን መሰረታዊ አረፍተ ነገር በትክክለኛነት ማዋቀር ይችላል | | | | | |
| | 2 | ተማሪው የተለያዩ ዓይነት የአረፍተነገር መዋቅርን ይጠቀማል | | | | | |
| | 3 | ተማሪው ስዋስዋዊ ትክክለኛ የሆነ አረፍተነገር በመመስረት ትርጉም እንዲሰጥ ያደርጋል | | | | | |
| | 4 | ተማሪው ከስህተት ነጻ የሆኑ አረፍተነገሮችን ማዋቀር ወይም መመስረት ይችላል | | | | | |
| | 5 | ተማሪው ትክክለኛ ስዋስዋዊ አረፍተነገርን ይጠቀማል | | | | | |
| ን በ ት | 1 | ተማሪው ተመሳሳይ ወይም ተዛማጅ እንዲሁም የማይመሳሰሉ ቃላትን ትክክለኛ ንበት ይጠቀማል | | | | | |
| | 2 | ተማሪው ጠብቀው እና ላልተው የሚነበቡ ቃላትን በአረፍተነገር ውስጥ ለይቶ ይጠቀማል | | | | | |
| | 3 | ተማሪው የተለያዩ አረፍተነገሮችን እንደየ አወቃቀራቸው የንባብ ቅላጼ ይጠቀማል | | | | | |
| | 4 | ተማሪው የሚያስተላልፈው መልእክት ሳይዛባ የተወሰኑ ሰዋሰወዊ ስህተቶችን ይሰራል | | | | | |
| | 5 | ተማሪው ሃሳብን በአረፍተነገር ውስጥ በማያያዝ በጥሩ ሁኔታ ይጠቀማል | | | | | |
| ፍሰት | 1 | ተማሪው ባልተገደበ ገለፃ ወይም አነጋገር ሃሳቡን መግለፅ ይችላል፡፡ | | | | | |
| | 2 | ተማሪው ትክክለኛ የድምጽ አወራረድና የቃላት ቅላጼን | | | | | |

| | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | በአግባቡ ይተገብራል፡፡ | | | | | |
| | 3 | የተማሪው ንግግር ጥርት ያለና ሀይል የማይፈልግ አፈ ፊት ተናጋሪን ይመስላል፡፡ | | | | | |
| | 4 | ተማሪው በትክክል የቋንቋውን ፍሰት ጠብቆ መናገር ይችላል፡፡ | | | | | |
| | 5 | ተማሪው የሚናገረው የቋንቋ ፍሰትን የጠበቀ ሆኖ በቋንቋው አፈ ፊት ተናጋሪ ዘንድ መልእክት ያዘለ ነው፡፡ | | | | | |

5 = እጅግ በጣምጥሩ 4 = በጣም ጥር 3 = ጥሩ 2 = ዝቅተኛ 1 = በጣም ዝቅተኛ

ሠንጠረዥ.1.ቃላዊ የመናገር ክሂል ግምገማ የትንተና ነጥቦችን ያሳያል፡፡ከላይ የተጠቀሱት ነጥቦች ቃላት ፣ሰዋስው ፣ ንበትና ፍሰት የሚባሉት አራቱ Brown ያስቀመጣቸው ቃላዊ የመናገር ክሂል መመዘኛዎች ናቸው፡፡በዚሁ መሰረት እያንዳንዳቸው 25% ነጥብን ይይዛሉ ይህ ማለት 4x25=100 ማለት ነው፡፡ በዚህ መሠረት በተሰጠው አመላካች ትልቁ ነጥብ መቶ ፐርሰንት ሲሆን በአጠቃላይ የግምገማው ውጤት በአራቱ ቃላዊ የመናገር መመዘኛ መስፈርት ላይ ተመስርቶ ቃላዊ የመናገር ምዘና ተሰጥቷል፡፡

### 2.1.3 የክርክር ምንነት

ክርክር ተግባቦታዊ ክሂላችንን የሚያዳብር ነው፡፡ የተቀናጀና የተዋቀረ ክርክራዊ ስልት ውጤታማ ነው፡፡ አድማጭን እያዝናና የሚያሳምን ነው፡፡ እንዲሁም በክርክር ወቅት የምናደርገው የአካል እንቅስቃሴና የድምፆችን ሁኔታ ለክርክራችን ክብደትን ይጨምርልናል፡፡ ክርክር የግለሰቦችን ሞራል፣ አድሎአዊነት የሚገልፅበት ሳይሆን ጥረት ያለ ስሜት የሚነገርበት ነው፡፡

Steinberg (2005) ሲገልፁ በክርክር ስልት ሂደት ውስጥ ከብዙ ክርክረዊ ነጥቦች ወደተፈለገው የሚወስደውን ሀሳብ ብቻ ላይ ማተኮር ነው፡፡ ክርክር ግላዊ ወይም ቡድናዊ ሁኔታዎችን ይዞ ቢቀርብም ይላሉ የአድማጭን አመለካከት ወደ ተከራካሪው ቡድን በማዘንበል ውሳኔ ለመስጠት የሚደረግ ሂደት ነው፡፡

Paulette dale and Jemes C Wolf (2000:28-31) ስለ ክርክር ስልት ሲናገሩ ክርክር የንግግሩን አውድ የሚመለከትና የተቃራኒውን አመለካከት በማየት ንግግር የሚደረግበት እና የሚከራከሩበት ነው፡፡

ክርክር እውነተኛ ነገር ላይ በመመስረት ጉዳዩን በትክክል ማስመሰል ነው፡፡ ክርክር የተማሪዎችን ሚና በበቂ ሁኔታ በማረጋገጥ የተለያየ አማራጮቻቸውን በመጠቀም ሳቢ በሆነ የመከላከል ስልት እውቀትን ማከፋፈል ነው፡፡ በስተመጨረሻም ከተፈለገው የክርክር ግባቸው ላይ በመድረስ የጉዳያቸውን ውሳኔ ድምጽ ማሰማት ነው፡፡

ክርክር ሰዎች ሊቀበሉህ የሚችሉትን መረጃ ይዞ በመቅረብ፣ አሳማኝ ክርክራዊ ስልትን ተጠቅሞ ሰፋ ያለ ማብራሪያ በመስጠት ለተቀመጡት ዳኞችና ለአድማጭህ ማብራራት ነው፡፡ ክርክር የተማሪዎችን የመናር ክሂል ለማሻሻል የሚያበረታታና ውጤታማ ትግበራ ስለሆነ ለከፍተኛ ደረጃ ተማሪዎችና መካከለኛ ደረጃ ላሉትም ተማሪዎች ተግባቦታዊ ክሂላቸውን ይጨምራል ተብሎ ይጠበቃል በማለት ፓውሌት ( 2000 2nd ed) ይገልጹታል፡፡

James (2000:32) የክርክር ጠቀሜታን በተመለከተ ክርክር በክፍል ውስጥ የተግባቦታዊና የውህዳዊ ዘዴዎችን በማራኪያዊ አተገባበር በማቅረብ የሚተገበር ነው፡፡ በመሆኑም ክርክር ለተማሪዎች እጅግ ብዙ ጠቀሜታዎችን ያበረክታል፡፡ ከነዚህም መካከል፡-

1. የተማሪዎችን አስተሳሰባዊ አድማስ ያሻሽላል፡- እያንዳንዱ ተማሪ በክፍል ውስጥ በሚቀርቡት ክርክራዊ አውድ ላይ የራሳቸውን ትንታኔ ሂስን ይሰጣሉ፡፡
2. የተማሪዎችን ተግባቦታዊ ክሂል ያዳብራል፡- ተከራካሪ አንድን ክርክር ለመናገርና ለማዘጋጀት ብሎም ክርክሩን ለማቅረብ በሚያቀናጃቸውና በሚለማመዳቸው ሰዓት የያዘውን ርዕስ ከህገራዊ አስፈላጊነቱ አኳያ ለመግለፅ ብዙ ሰዓቶችን ይወስድበታል፡፡ በዚህም የቃላት ክምችቱ ያድጋል የአስተሳሰብ አድማሱ ይሰፋል፡፡
3. ጥያቄያዊ ክሂልን ያዳብራል:- በክርክሩ ሂደት ወቅት አብዛኛውን ጊዜ ከሚገጥማቸው ውስጣዊና ውጫዊ የመሸነፍና የማሸነፍ ድል መነሳት ጥያቄን እንዲፈጥሩ ያዘጋጃቸዋል፡፡

4. የክርክር ሂደት ተማሪዎችን በሚማሩት ትምህርት ትርጉም ባለው መንገድ የሚረዳ ብቻ ሳይሆን ከማህበራዊ ህይወታቸው ጋርም የሚቆራኝና የመለያየትን ስሜት የሚቋቋም በመሆኑ ህዝባዊ ስሜትን ይፈጥራል፡፡
5. ፖሊሲያዊ ክርክር በተለይ ተማሪዎችን ብዝሃ አመለካከታቸውን እንዲገልፁ በማስተማር የጋራ ችግራቸውን እንዲያቃልሉ በማድረግ የመናገር ክሂላቸውን ያዳብራል፡፡

ከላይ የሚታየው ጠቀሜታ ላይ በመመስረት በክፍል ውስጥ መናገርን በክርክር መለማመድ አስፈላጊ ነው፡፡ ይህ ደግሞ የተማሪዎችን የመናገር ክሂልን ለማሻሻል የሚመረጥና ተስማሚ ነው ይላሉ ፡፡

### 2.1.3.1 በክርክር የመናገር ክሂልን የማስተማር አስፈላጊነት

በክርክር የማስተማርን ስልትን በተመለከተ Maryadi (2008:16) ሲገልፁ ‹‹ ክርክር የተማሪዎችን አስተሳሰብ ለበለጠ የሚያነሳሳ ከመሆኑም በላይ ተማሪዎቹ አቋማቸውን ሲገልጹ ወይም ከተቃራኒያቸው የሚመጣውን ሀሳብ ወይም አስተያየት በራስ መተማመን ይመልሱታል፡፡›› ይህ ዓይነቱ ለተከራካሪው አካል ብቻ ሳይሆን ሁሉንም ተማሪዎች ጥሩ ተሳታፊ ያደርጋቸዋል ይላሉ፡፡

የተማሪዎችን የመናገር ክሂል ውጤታማ ከሚያደርጉት የማስተማሪያ ዘዴዎች አንዱና ዋነኛው ክርክር ነው፡፡ በመሆኑም የክርክር አስፈላጊነት እና ጠቃሚነትን Bambang (2006:125) ክርክርን እንዲህ ሲሉ ይገልፁታል ‹‹ ክርክር የተሰጠውን ርዕስ እንኳ ለመረዳት የሚጠቅም እንቅስቃሴ ነው ይላሉ፡፡ ክርክር በሁለት ቡድን የሚዘጋጅ ነው፡፡ እያንዳንዱ ቡድን 3-5 ተማሪዎችን የሚያቅፍ ነው ፡፡ ‹ደጋፊ‹ እና ‹ተቃራኒ‹ ቡድን ሆነው ይመሰረታሉ›› Kirieger(2005:1) ክርክርን እንዲህ ሲሉ ይገልፁታል ‹‹ክርክር ለቋንቋ ትምህርት እጅግ በጣም ጥሩ እንቅስቃሴ የያዘ ነው፡፡ ምክንያቱም ይላሉ ተማሪዎችን ለጥሩ ስነልሳናዊ አካሄድና ለተለያየ አስተሳሰባዊ እድገት ያዘጋጃቸዋል›› በማለት ዘዴውን ያብራሩታል፡፡

Shan (2005:21) ደግሞ በክርክር የማስተማር ዘዴን እንዲህ ይገልፁታል ‹‹ሁለት ቡድኖች በሁለት ተቃራኒ ጉዳዮች ላይ በመወያየት በማያስማማ ጉዳይ ግን በሚያስማማ ህግ ላይ ተመስርተው፤ ሁለቱም የሚሰጣቸውን የክርክር ውሳኔ በማዳመጥ በቀረበው ምክንያታዊ ውጤት እና ማስረጃ አሸናፊ የሆነውን ይመርጣሉ፡፡››በማለት ያስረዳሉ፡፡

ከላይ በተሰጡት ገለፃዎች መሰረት አጥኚው የተሠጡትን የክርክር ሀሳቦች በማጠናከር በዚህ ጥናት ክርክር ሃሳብን ለመግለፅና ለማብራራት እንዲሁም ሁለቱ ተቃራኒ ቡድኖች እራሳቸውን ለመከላከል ሲሉ የሚያደርጉት ምልልስ የመናገር ክሂልን ለማዳበር ከፍተኛ ሚና እንዳለው ለማየት ችሏል፡፡

### 2.1.3.2 የክርክር ንድፎች

Saraha, (2015፡27) Goodnight, (1993፡16) ዋቢ በማድረግ እንደገለጸችው የተለያየ ስልተ አተገባበር ያላቸው የክርክር ንድፎች እንዳለ ትጠቅሳለች፡፡ ከእነዚህም፡-

- ሀ. **መደበኛ የክርክር ንድፍ፡-** ይህም ንድፍ ለጀማሪ ተከራካሪዎች የሚያገለግል ነው፡፡
- ለ. **አቋራጭ ፈታኝ ንድፍ**፡- ሲሆን በሁለተኛና በኮሌጅ ደረጃ ጥቅም ላይ የሚውል የክርክር ንድፍ ነው፡፡
- ሐ. **የሊነክሎን ዳግላስ ንድፍ**፡- ይህም ተጽእኖ አሳዳሪ ውጤቶችን ለመከራከር የሚነደፍ ታዋቂ ንድፍ ነው፡፡
- መ. **ቀላል የክርክር ንድፍ፡-** ሲሆን ይህም በአብዛኛው ለኢ- አፈፊት ጥቅም ላይ የሚውል ነው፡፡

በዚህ ጥናትም ቀላል የክርክር ንድፍ ጥቅም ላይ ውሏል፡፡ አጥኝው ይህንን የክርክር ንድፍ የተጠቀመበት ምክንያት የሁለት ቡድን ክርክር በመሆኑና በቅድመ ፈተና ማጣራት በተገኘው ውጤት መሰረት የተማሪዎቹ የመናገር ችሎታ ደካማ ሆኖ በመገኘቱ ነው፡፡

### 2.1.3.3 ቀላል የክርክር ንድፍ

Saraha (2015፡37) Lustigova (2011)ን በመጥቀስ ቀላል የክርክር ንድፍ ደጋፊ የቡድን ንግግርን፣ ተቃራኒ የቡድን ንግግር፣ ተቃራኒ ቡድን መመሪያ፣ ከታዳሚዎችና ከቡድኖች የሚመጣ፣ ጥያቄና የሚሰጥ መልስ፣ ደጋፊ መዝጊያ አስተያየት፣ ተቃራኒ የመዝጊያ

አስተያየት፣ ታዳሚዎች አሳማኝ ሐሳቦችን ይፈትሻሉና መምህሩ ገንቢ ምጋቤ ምላሽ ይሰጣል የሚሉትን ነጥቦችን ያካትታል፡፡

ሥነዘዴውም እንደ Saraha (2015; 38) Lustigova (2011)ን ዋቢ በማድረግ በመካከለኛና በዝቅተኛ የክፍል ደረጃዎች መናገርን በክርክር ዘዴ ስናስተምር የተማሪዎች የመናገር ክሂል ይዘት ላይ በማተኮር የመናገር ክሂላቸውን በማሻሻል ላይ አጽንኦት የሚሰጥ ነው፡፡

ቀላል ክርክርን ስንመዝን በሐሳብ አደረጃጀት፣ አስታየቶችን የመጠቀም፣ ምሳሌዎችንና፣ መረጃዎች ላይ ማተኮር፣ ከቋንቋ አጠቃቀም እይታ አንጻር ምጋቤ ምላሾችን መስጠት፣ ቋንቋ እንዴትና ለምን እንደተጠቀሙ፣ የአስተያየት መስጫ አመላካች ሐረጋት መሻሻሉን ፣መልካም ግንኙነትን የመፍጠር ስልትና ግላዊ አስተያየቶችን በውጫዊ መረጃዎች ማጠናከርን ከግምት ውስጥ ማስገባት ይኖርብናል፡፡

### 2.1.3.4 የክርክር ክፍሎች

በክርክር ስልታዊ ዘዴ ውስጥ፣ የተወሰኑ ክርክራዊ ሂደት አይነቶችን እናገናኛለን፡፡ እነዚህም የሂደት አይነቶች Joe Bellon (2000. Vol 36) ላይ ከክርክር ስልታዊ ዘዴ ጋር የሚዛመዱትን እንደሚከተለው ይገልፁታል፡፡

1. **እንቅስቃሴ**

የክርክሩ ርዕስ እንቅስቃሴ ቢሆን አብዛኛውን ጊዜ አንድ መሪ ተዋናይ ሆኖ የምናገኘው የቃላቱን እንቅስቃሴ ነው፡፡ ምሳሌ ‹ቤቱ የሚያምንበት‹ ወይም ይህ ቤት ያመነበት፣ ሁለቱም አሉታዊና አዎንታዊ የሆኑት ቡድኖች አድሎአዊ ባልሆኑ የእንቅስቃሴ ቃላትን በመጠቀም ክርክርን ያካሂዳሉ፡፡ አከራካሪ ነው ማለት እንቅስቃሴው መታመን የማይችልበት መንገድ የተገለፀ ነው ማለት ነው፡፡ አድላዊነት የሌለው ነው ማለት እንቅስቃሴው ለሁለቱም ወገን ሳያዳላ በነፃነት የቆመ ማለት

2. **ጭብጣዊነት**

በእንቅስቃሴው ላይ መስማማት ወይም አለመስማማት ሲሆን ምክኒያታዊ ጉዳዩ ጠንካራ መሠረት ያለው ሁሉንም መሸፈን የሚችል መዋቅራዊ ይዘት ያለው መሆን አለበት፡፡

ጭብጥነት ማለት የተነሳውን ትልቅ ጥያቄ ለመመለስ ለምን ብሎ ጥያቄ የሚያነሳ ነው፡፡ የቤቱ አንዱ ክፍል እንቅስቃሴውን ይደግፋል ወይም ይቃወማል ጭብጥ ማለት ቡድኑ ሊያረጋግጥ የፈለገው ነገር ማለት ነው፡፡

3. **አለመግባባት /argument/**

ክርክር እያንድአንዱ ቡድን በራሱ ሀሳብ ለይ አቋምን በመያዝ የተቃራኒውን ቡድን ለመርታት የጦርነት ያክል ተጋድሎአዊ ምልልስን የሚያደርጉበት ስፍራ ነው፡፡ በሂሳዊና መሠረታዊ አስተሳሰብ በመጠቀም አስደናቂና ዋጋ ያለው ስፍራ መስራት ይቻላል፡፡ አለመግባባት ማለት በተለያየ ሀሳብ ውስጥ ያለን ይዘት መደገፍ ማለት ነው፡፡

4. **ገለፃ**

ተከራካሪ አንድ አለመግባባትን ለመርታት የሚፈልገውን ጠንካራ ምክንያት ይዞ መቅረብ ብቻ ሳይሆን አለመግባባትን ወይም ክርክርን ለመርታት የተቃዋሚውን ሀሳብ በተለያየ መንገድ ማዳከምና መርታት አይነተኛ ባህሪ ነው፡፡

5. **መደምደሚያ**

መደምደሚያ ማለት የተባለውን ነገር ጠቅለሎ በአጭሩ ማቅረብ ሲሆን ጥሩ ማጠቃለያ ግን ተመራጭነት አለው፡፡ ክርክር ከመጀመሩ በፊት አንድ ተከራካሪ ጥሩ ተከራካሪ ለመሆን በክርክሩ ርእስ ዙሪያ ለከራከርባቸው ወይም ሊያነሳ የፈለጋቸውን ነጥቦች በቅድመ ተከተል ሊያውቃቸው ግድ ይሏል፡፡ ክርክር ብዙውን ጊዜ ስኬታማነቱ ተስፋ የሚደረግበት ነው፡፡

### 2.1.3.5 **የክርክራዊ ስልት ቅደም ተከተል፡-**

Rubiati (2010:19) ሲገልፁ ክርክራዊ ስልታዊ ትግበራ የተለያዩ ቅርፅን ይዘው የሚራመዱ ናቸው ይላሉ፡፡ በንግግር ክፍል ውስጥ ክርክር የሚከተሉትን መመሪያዎች ቅደም ተከተልን ይከተላሉ ይላሉ፡፡ እነሱም፡-

1. ተማሪዎችን በተለያየ የቡድን መጠን መከፋፈል፡፡ እያንዳንዱ ቡድን ቢበዛ 5-6 ተማሪዎችን ይይዛል፡፡
2. የክርክሩን ርዕስ መምረጥ፣ ለቡድኑ ርዕሱን መስጠት (ማመልከት)

3. ተሳታፊዎች በቂ የሆነ መረጃ ይዘው መቅረባቸውን ክርክሩ ከመጀመሩ በፊት ዝግጁ መሆናቸውን ማረጋገጥ
4. ርዕሱን ማስተዋወቅና ክርክሩን ማቅረብ
5. የሚከተሉትን የክርክር አቀራረብ ምሳሌዎች ናቸው፡፡
   ሀ. አንደኛው ወገን፡- አመለካከቱን በንግግር በመክፈት ለቡድኑ አባላት መግለጫ ይሰጣል፡፡
   ለ. ሁለተኛው ወገን፡- ለአለመግባባቱ በንግግር በመክፈት ለቡድኑ አባላት መግለጫ ይሰጣል፡፡
   ሐ. አንደኛ ወገን - ሀሳቡን የመግለፅ ዕድል አለው፡፡
   መ. ሁለተኛ ወገን - ሀሳቡን የመግለፅ እድል አለው፡፡
   ሠ. አንደኛ ወገን - ለሁለተኛ ጊዜ ሀሳቡን የመግለፅ እድል
   ረ. ሁለተኛ ወገን - ለሁለተኛ ጊዜ ሀሳቡን የመግለፅ እድል
   ሰ. አንደኛ ወገን - ሀሳብን የማጠቃለያ ጊዜ ይወስዳል
   ሸ. ሁለተኛ ወገን - ሀሳብን የማጠቃለያ ጊዜ ይወስዳል

### 2.1.3.6 የክርክራዊ ስልት ትምህርት ዓላማዎችና ጠቀሜታቸው፡-

ክርክራዊ ስልት ትምህርትን ለመናገር ክሂል መጠቀም የተለያዩ ጠቀሜታዎቸ አሉት በማለት Rubiati (2010; 20 ) እንደሚከተለው ይግልጻቸዋል፡፡

1. ክርክራዊ ስልት በክፍል ውስጥ ፍጹም የማይናገሩ ተማሪዎችን እንዲሳተፉ ያበረታታቸዋል፡፡
2. ክርክር ለተማሪዎች ከፍትኛ የመሳተፍ አጋጣሚን በመፍጠር ከመሰረታዊ የትምህርት ርእስ ባሻገር የእውቀት ልምምድን ከክርክር ትምህርቱ ያገኛሉ፡፡ጥሩ ተከራካሪም ለመሆን ራሳቸውን ያዘጋጃሉ፡፡ Elliot, L. (1993)፡፡
3. ተከራካሪዎች የሚከራከሩትን ጉዳይ በመተንትን ፣በማጠንከር እና በመገምገም ለተቃራኒ ቡድን የሚሰጡትን መልስ በእውቀት ያስደግፋሉ፡፡Vygotsky ,(1978)፡፡
4. ክርክር የተማሪዎችን የምርምር ክህሎት ለማዳበር ይረዳል ፡፡

5. ተማሪዎች ከክርክር ትምህርቱ ከፍትኛ ተጠቃሚ በመሆን የመሪነት ፍላጎት ያድግባቸዋል፣ እንደገናም ጥያቄዎችን በመመልስ የአሸናፊነት ስሜት በሌሎች ውስጥ ያሳድራል ፡፡Goodnight ,(1993)፡፡
6. ክርክራዊ ስልት ትምህርት አርቆ የማሰብ አቅምን ያዳብራል፡፡
7. ክርክር ውጤታማ የመናገር ክሂልን ያሳድጋል፣እንደገናም ተከራካሪዎች ቀደም ሲል በታዳሚ ፊትለፊት የመናገርና የመወሰን ፍርሃት የነበረባቸውን ሁኔታ ተቃራኒ ቡድናቸውን ለመርታት በሚያደርጉት ፍልሚያ እና በሚሰጡት ገለጻ ራሳቸው ሳያስቡ የመናገር ክሂላቸው እንዲዳብርላቸው ይረዳችዋል፡፡Ericson & Murphy ,(1987) Byrne elal ,(1993 )፡፡
8. ክርክር የቡድን ወይም የጋራ ህብረት ክህሎትን ያዳብራል ፡፡ክርክር የፉክክር እንቅስቃሴ ወይም ትግበራ የሚደረግበት ሂደት በመሆኑ ተከራካሪዎች በክርክር ብቁ ለመሆን ጥረት ያደርጋሉ እግረ መንገዳቸውንም የመናገር ክሂላቸውን የሳድጋሉ፡፡Williams , (2001)፡፡
9. ክርክራዊ ስልት ትምህርት ተግባቦታዊ ክህሎትን ያዳብራል፡፡

በአጠቃላይ ከላይ የተጠቀሱት ክፍሎች የመናገር ክሂልን እና ክርክራዊ ስልት ትምህርት አተገባበር ላይ በማተኮር የመናገር ክሂልን ለማዳበር የምንማርበት መንገድ በከፍተኛ ደረጃ ያሳዩን ነበር፡፡መምህራን የተማሪዎችን የመናገር ክሂል ለማሻሻል ጥሩ አጋጣሚ ያገኙበት የትምህርት ክፍል ነው፡፡ምክንያቱም ክርክራዊ ስልት ትምህርት ትግበራ በተማሪዎች ዘንድ የተለየ አጋጣሚን በመፍጠር በጋራ የሚሰሩበትን ሁኔታ ያበረታታል፡፡በክፍል ውስጥም የሃላፊነትን ስሜት እንዲገነዘቡ ይረዳቸዋል፡፡የክርክራዊ ስልት ጥናት ውጤታማነትን በማለማመድ አርቆ የማሰብ አቅምን በማሳደግ ቃላዊ የመናገር ክሂልን ያዳብራል ፡፡

ከዚህም በተጨማሪ ይህ የክርክር ስልት አዎንታዊ ውጤትን በተማሪዎች ዘንድ በማሳየት የተማሪዎችን ግላዊ ዝግጅትና ተሳትፎ ያጠነክራል፡፡ይህ በተለያየ ክርክራዊ ስልት የማስተማሪያ ዘዴ ተማሪዎችን በክፍል ውስጥ በማነቃቃት የመናገር ክሂላቸው እንዲዳብር ከፍተኛ አስተዋፅኦ አለው፡፡ በመጨረሻም መምህሩ የተመቻቸ አካባቢን ወይም ሁኔታን በትምህርት ቤት ውስጥ በመፍጠር ተማሪዎች አዎንታዊ በሆነ መልኩ የመናገር ክሂላቸውን የሚያዳብሩበትን መንገድ ማመቻቸት ጠቀሜታው ከፍ ያለ ነው፡

## 2.2 የተዛማጅ ጽሑፍ ቅኝት

በዚህ ንዑስ ርእስ ስር በቀጥታ በሀገርኛ የተሰሩ የተዛማጅ ጽሑፍ ጥናቶችን አጥኝው ባደረገው ፍተሻ ከዚህ ጥናት ርእስ ጋር የሚዛመድ ሊያገኝ አልቻለም፡፡ይሁን እንጅ በከፊል የተወሰኑ በአማርኛ የመናገር ክሂል አተገባበር ላይ የተሰሩ ጥናቶች መካከል ለመቃኘት ሞክሯል፡፡

በመናገር ክሂል አተገባበር የማስተማር ዘዴ ከተሰሩ ጥናቶች ከበደ (2000)፡፡ "በአማርኛ ትምህርት ክፍለ ጊዜያት የመምህር ተማሪ ንግግር ልውውጥ ትንተና" በሚል ርእስ በደብረብርሃን ትምህርትና ሙያ ማሰልጠኛ ኮሌጅ ባደረገው ጥናት ዓላማ አድርጎ የተነሳው በአማርኛ የትምህርት ክፍለ ጊዜያትን የመምህር ተማሪ የንግግር ልውውጥ መተንተን ነው ፡፡ይህንንም ለማረጋገጥ የአማርኛ ቋንቋ መምህራንን የክፍል ውስጥ ትግበራ ለስድስት ክፍለ ጊዜያት የክፍል ውስጥ ምልከታ በማከሄድ በመምህርና በተማሪዎች መካከል የሚደረገውን የንግግር ምልልስ በጥናቱ ሲያሳይ የመምህሩ ተራዊ ንግግሮች አንጻራዊ ርዝመት እንዳላቸውና የተማሪዎች የንግግር ጊዜ ዝቅተኛ በመሆኑ ተማሪዎች የንግግር ክሂላቸውን ስለማይችል ሰፊ ጊዜን ለተማሪዎች መስጠቱ አማራጭ ነው በማለት አሣይቷል፡፡

መንግስቱ (1997)፡፡ "በአዲስ አበባ መስተዳድር የዘጠነኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ ትምህርት የክፍል ውስጥ የመናገር ክሂሊ የማስተማር ዘዴ አተገባበር ግምገማ" በሚል ርእስ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ባደረገው ጥናት ዓይነታዊ ገላጭ የምርምር ዘዴን በመጠቀም በዋናነት መሰረት አድርጐ የተነሳው መምህራን በክፍል ውስጥ መናገርን ለማስተማር የሚጠቀሙትን ዘዴ በምልክታ በቃለ መጠይቅ ማረጋገጥና መፍትሄ ማስቀመጥ እንዲሁም ጠንካራ እና ደካማ ጎኑን መገምገም ነው ፡፡በመጨረሻም የደረሰበት ውጤት መምህራን ተማሪዎችን ለመናገር የሚጋብዝ የማስተማሪያ መርጃ መሳሪያዎች እና ይዘቶችን አለመጠቀማቸው ተማሪዎች ሀሳባቸውን የመግለጽ ችሎታቸውን የማያዳብር የርስ በርስ መስተጋብር ለመፍጠር የማያስችል መሆኑን፣ ይህ ደግሞ የመናገር ክሂልን የማያዳብር እንደሆነ ሲገልጽ መምህራን የመናገር ክሂልን በተማሪዎች ዘንድ ለማሳደግ የተለያዩ የማስተማር ዘዴዎችን መጠቀም እንዳለባቸው ይጠቁማል፡፡

እንዲሁም አብራሃም (2003)፡፡ በጥናቱ አላማ አድርጎ የተነሣው "የመናገር ክሂል ትምህርት አቀራረብ የማስተማሪያ ዘዴ ምርጫና ትግበራ ከዘመናዊው ጋር ተጣጥሞ በክፍል ውስጥ መቅረብ አለመቅረቡን መገምገም" የሚል በአፋር ክልል በተመረጡ ሁለተኛ እርከን ትምህርት ቤቶች ላይ ጥናቱ በገላጭ የምርምር ዘዴ የተካሄደ ሲሆን ፤ በዚሁ መሰረት አብራሃም በክፍል ውስጥ ባደረገው ምልከታ እና ከጽሁፍ መጠይቅ ባገኘው መረጃ መሠረት አብዛኛዎቹ መምህራን በክፍል ውስጥ የመማር ማስተማሩን ሂደት በጥንድ ወይም በቡድን ሥራ እንዲታገዝ አለመሞከራቸው፣ በቋንቋው ተጠቅመው በመናገር ሀሳባቸውን በነጻ የሚገልጹበትን ሁኔታ አለማመቻቸታቸው፣ የንግግር ማስተማሪያ ደረጃዎችን በተገቢው መንገድ አለማከናወናቸው፤ በተጨማሪም ከመማሪያ መጽሐፉ ጎን ለጎን የተማሪዎችን የመናገር ፍላጎት ሊያነሳሳ የሚችል ተግባር በጥንቃቄ አለመመረጡ፣ ለሁሉም ተማሪዎች እኩል እድል አለመሰጠቱ የተማሪዎችን የመናገር ክሂል መዳበር አለመቻሉን አሣይቷል፡፡

ሌላኛው እጅጉ (2003)፡፡ በጥናቱ የተመለከተው "በደብረብርሃን ከተማ በተመረጡ ሦስት የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሰባተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የመናገር ክሂል አቀራረብ ግምገማ" በገላጭ የምርምር ዘዴ ፣ ምልከታን እና የጽሁፍ መጠይቅን በመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያነት በመጠቀም የቋንቋ መምህራን የመናገር ክሂል የማስተማር ዘዴን እንዴት እያቀረቡ እንደሆነ እና በአቀራረቡ የታዩ ችግሮችን እንዲሁም የችግሮችን መንስኤዎች በመለየት የመፍትሔ ሐሳብ በመስጠት ግምገማ አካሂዷል፡፡በዚሁ ጥናት መሰረት መምህራን በመማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የተጠቀሱትን የንግግር መማሪያ ዘዴዎች አለመተግበራቸው የተማሪዎች የመናገር አቅም መቀጨጨን አይቷል፡፡በጥናቱም መምህራን የመናገር ክሂልን ለማስተማር በመማሪያ መጥሐፉ ያሉትን እንዲሁም ተጨማሪ ስልቶችን አክለው በያቀርቡ የተማሪዎች የመናገር ክሂል ሊዳብር እንደሚችል በመፍትሄ ሀሳቡ አስቅምጧል፡፡

በአጠቃላይ ከላይ ያየናቸው ጥናታዊ ጽሑፎች በክፍል ውስጥ የአማርኛ ቋንቋ የመናገር ክሂል አተገባበር፣የተማሪዎችንና የመምህራንን የክፍል ውስጥ በንግግር ላይ ያላቸውን መስተጋብር ማየትና እንዲሁም መናገርን የማስተማሪያ ስነዘዴ በክፍል ውስጥ ያለውን የመማር ማስተማር ሂደት ደካማ ጎኑን እና ጠንካራ ጎኑን ማወቅና በጥናት ማረጋገጥ ከዛም የመፍትሄ ሀሣብ ማስቀመጥ ነው፡፡በመሆኑም ከላይ የተጠቀሱት ጥናቶች የመናገር ክሂልን

አተገባበር የሚያመላክቱ ቢሆኑም ይህ ጥናት ከተጠቀሱት ጥናታዊ ጽሁፎች የሚለየው በክርክራዊ ስልት የመናገር ክሂልን በማስተማር ውጤታማነቱን መፈተሽ በመሆኑ ነው፡፡

ሌላው በቀጥታ መናገርን በክርክራዊ ዘዴ የማስተማር ውጤታማነት ፍተሻ ጋር ተዛማጅነት ያላቸውን የውጭ ሀገር ጥናታዊ ጽሁፎች እንደሚከተለው ተዳሰዋል፡፡

የመጀመሪያው በ Junaidi, (2011) 'በኒጀር ሹርካታ ስበላ ማሬት' ዩኒቨርሰቲ የተሰራ ጥናታዊ ጽሆፍ ነው፡፡ የጥናቱም አላማ ረቂቅ ክርክር ስልት የተማሪዎችን የመናገር ክሂል ያሻሽላል ወይስ አያሻሽልም የሚለውን መመርመር ነው፡፡ መረጃዎችም በሰነድ ፍተሻ ፣ በምልከታ፣ በቃለ መጠይቅና በጽሁፍ መጠይቅ ተሰብስበዋል፡፡ በመጠናዊና በአይነታዊ ዘዴ በመጠቀም የተገኘው የጥናቱ ውጤት የሚያመላክተው ረቂቅ ክርክራዊ ስልት የተማሪዎችን የንግግር አቅማቸውን ፣ ተሳትፏቸውን ፣ የመደናነቅና መቻቻልን ፣ መነሳሳትና ፍላጎትን ፣ አዕምሯዊ መነቃቃትን እና ሒሳዊ አስተሳሰባቸውን እንዳሻሻለ ነው፡፡ በአጠቃላይ ረቂቃዊ ክርክር ስልት የተማሪዎችን የመናገር ክሂል በማሳደግ በጣም አስፈላጊና ስኬታማ ስልት መሆኑን አረጋጠዋል፡፡

ይህ ጥናት ከJunaidi, (2011) ጥናት ጋር የሚያዛምደው ሁለቱም የክርክር ውጤታማነት የመናገር ክሂል ከማሻሻል አንጻር የፈተሹ ናቸው፡፡ የሚያለያያቸው ጉዳይ ደግሞ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ነው፡፡ ይህም በጁናኢድ ቃለ መጠይቅ ፣ የጽሁፍ መጠይቅ፣ ሰነድ ፍተሻ ጥቅም ላይ ሲውሉ በዚህ ጥናት ግን ፈተናና ምልከታ ብቻ ጥቅም ላይ ውለዋል፡፡

ሁለተኛው በRicha (2010) በ ( IAIN ) በዋሊሶንግ ግዛት በክርክር ስልት የመናገርን ክሂል ማሻሻል ላይ የተሰራ ጠናት ነው፡፡ አላማውም የመናገር ክሂልን ለማስተማር የክርክር ስልት ትግበራና የተማሪዎች የመናገር ክሂል እንዴት እንደተሻሻለ መፈተሽ ነው፡፡ መረጃዎችም በምልከታና በፈታና ተሰብስበዋል፡፡ የጥናቱም ውጤት የክርክር ስልት የተማሪዎችን የመናገር ክሂል እንዳሻሻለ አመልክቷል፡፡

የ Richa, (2010) ጥናት ከዚህ ጥናት ጋር የሚያዛምደው ሁለቱም ጥናቶች የመናገር ክሂልን በማሻሻል ረገድ የክርክር ውጤታማነት የሚፈትሹ ናቸው፡፡ ይሁንና በጥናቱ ተሳታፊዎች ላይ ልዩነት አላቸው፡፡

ሦስተኛው ተዛማጅ ጽሁፍ በSaraha (2015) "በጋዛ አል-አዝሀር ዩኒቨርሲቲ የመናገር ክሂል በማሳደግ ረገድ የክርክርን ውጤታማነትን መፈተሽ ነው፡፡" የጥናቱም አላማ የመናገር ክሂልን በማሳደግ የክርክርን ውጤታማነት መፈተሽ ነው፡፡ ጥናቱም ፍትነታዊ ሙከራዊ ዘዴን የተከተለ ነው፡፡ መረጃዎችም በፈተና ብቻ ተሰብስበዋል፡፡ በስታተስቲክስ የዊልክሰን ምዘና ውጤት መሰረት በቅድመና በድህረ ፈተና መካከል ጉልህ ልዩነት እንዳለ አመላክቷል፡፡

የ Saraha, (2015) ከዚህ ጥናት ጋር የሚያዛምደው ሁለቱም ጥናቶች የክርክር ውጤታማነትን የመናገር ክሂልን በማሻሻል ረገድ ያለውን ሚና የፈተሹ ናቸው፡፡ የሚለያዩትም በመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያቸው ነው፡፡ ይህም በ Saraha, (2015) ፈተና ብቻ ለመረጃ መሰብሰቢያነት ሲውል፣ ይህ ጥናት ግን ፈተናና ምልከታን ተጠቅሟል፡፡ ይህም የጥናቱን ጥንካሬ ልዩነት ያሳያል፡፡

በአጠቃላይ ይህ ጥናት ከነዚህ የውጭ ሀገር ጥናቶች ጋር መናገርን በክርክር ስልት በማስተማር ተመሳሳይነት ቢኖረውም አጥኚው በራሱ አካባቢ ተማሪዎች ላይ መናገርን በክርክር ስልት ማስተማሪያነት በመጠቀም ሊመጣ የሚችለውን የመናገር ክሂል ለውጥ ለመፈተሽ ያስችለዋል ማለት ነው፡፡

# ምዕራፍ ሦስት

# የአጠናን ዘዴ

ይህ ጥናት ፍትነታዊ ሲሆን የጥናቱ ዋና ዓላማ በክርክራዊ ዘዴ አተገባበር አማካኝነት የመናገር ክሂልን ማስተማር በተማሪዎች ውጤታማነት ረገድ ያለው አስተዋጽኦ ምን ይመስላል? የሚለውን መፈተሽ ነው፡፡ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎችን የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በዚህ መሰረት ጥናቱ ከታለመው ግብ ላይ ይደርስ ዘንድ አሃዛዊ እና የዓይነታዊ የምርምር አካል የሆነውን ገላጭ ምርምርን መሠረት በማድረግ የተማሪዎችን የፈተና ውጤት በስታቲክሣዊ ስልት መሠረት ተተንትኖ ቀርቧል፡፡ በመሆኑም ጥናቱ በሙከራዊ ቡድኑ እና በጥብቅ ቡድኑ ውጤት መካከል ያለውን ተቀራራቢነትና ልዩነት በንጽጽር አሳይቷል፡፡ ጥናቱም በሊሙ ገነት ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የሚማሩ የ2009 ዓ.ም የ9ኛ ክፍል ተማሪዎችን ተተኳሪ በማድረግ ተካሂዷል፡፡

## 3.1 የጥናቱ ተሳታፊ ተማሪዎች

ጥናቱ የተተኮረባቸው ተሳታፊዎች በኦሮሚያ ክልል በጅማ ዞን በሊሙ ኮሳ ወረዳ በሊሙ ገነት ከተማ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በ2009 ዓ.ም የሚማሩ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ናቸው፡፡ በወረዳው ካሉት አምስት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መካከል አጥኚው የሊሙ ገነት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤትን በዓላማ ተኮር የናሙና አመራረጥ ስልት መርጧል፡፡ምክንያቱም አጥኚው ለዚህ ጥናት ትክክለኛነት አንድ ትምህርት ቤት ላይ ብቻ መስራቱ በቂ ሆኖ በማግኘቱ እና እንዲሁም መደበኛ ስራውን የሚያከናውንበት ትምህርት ቤት በመሆኑ ለጥናቱ የሚያስፈልጉ መረጃዎችን ማግኘት ያስችላል ተብሎ በመታመኑ ነው፡፡ይህም በመሆኑ ከዚህ ትምህርት ቤት ተገቢውን መረጃ የማግኘቱ እድል አጥኚው ሰፊ ሆኖ አግኝቶታል፡፡

በሊሙ ገነት ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች የሚማሩባቸው 20 ክፍሎች ሲሆኑ፣ ከነዚህ 20 ክፍሎች መካከል ጥናቱ ፍትነታዊ በመሆኑ የሙከራ እና ጥብቅ ቡድን የሚሆኑ ሁለት ቡድኖች ተወስደዋል፡፡ በመሆኑም ጥናቱ በተራ የእጣ ናሙና ስልት ሁለት ክፍሎችን በመውሰድ ተተግብሯል፡፡ በመጀመሪያ እጣ የወጣለት ዘጠነኛ 'B' ሙከራዊ ቡድን ሲሆን በሁለተኛ ደረጃ እጣ የወጣለት ክፍል ዘጠነኛ 'L' ደግሞ ጥብቅ ቡድን ሆነዋል፡፡ በመሆኑም የክፍሉን ቁጥር እንደዚህ መወሰን ያስፈለገው ጥናቱ በሙከራ ላይ

የተመሠረተ በመሆኑ አስተማማኝነቱንና ተገቢነቱን ለመጠበቅ ነው፡፡ የክፍሉ ደረጃውም የተመረጠበት ዋና ምክንያት መረጃውን በትክክል ለማጠናከር ከ 10ኛ ክፍል ይልቅ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች መደበኛ የመማር ማስተማር ሂደት ላይ ስለሚገኙ ነው፡፡ ይህ ማለት የ10ኛ ክፍል ተማሪዎች ሀገር አቀፍ ፈተና ተፈታኝ ስለሆኑ ከዝግጅትና ጊዜ መጣበብ አንጻር ሁኔታዎች የተመቻቹ ስለአልነበሩ በጥናቱ ሊካተቱ አልቻሉም፡፡

ከሁለቱ ከተመረጡት ቡድኖች ውስጥ እንድገና በተራ እጣ ናሙና ለሙከራ ቡድኑ ከዘጠነኛ ' B ' ክፍል ተማሪዎች ውስጥ ወንድ 8 ሴት 8 ድምር 16 ተማሪዎችን ለጥብቅ ቡድኑ ከዘጠነኛ ' L ' ክፍል ውስጥ ወንድ 8 ሴት 8 ድምር 16 ተማሪዎችን ባጠቃላይ ወንድ 16 ሴት 16 ድምር 32 ተማሪዎችን መምረጥ ተችሏል፡፡ ይህም የሆነበት ምክንያት በጥናቱ ቃላዊ ፈተና ለማካሄድ ቁጥራቸውን እንዲህ መመጠኑ የጥናቱን አስተማማኝነቱንና ትክክለኛነቱ ለማረጋገጥ ይረዳል በማለት ያለው (2004፣139) በፍትነታዊ ሙከራዊ ጥናት ላይ የተሳታፊዎች ቁጥር ሊወሰን እንደሚገባ ያስረዳል፡፡

### 3.2 የሙከራዊ ቡድኑ የክፍል ውስጥ ክንውን ናሙና

ሙከራዊ ቡድኑና ጥብቅ ቡድኑ ከተለያዩ በኋላ አጥኚው ሁለቱንም ክፍሎች በተከታታይ ለሁለት ወር ለስምንት ዙር አስተምሯል፡፡ የሙከራዊ ቡድን ተማሪዎች በክርክራዊ ዘዴ ንግግርን የተማሩ ሲሆን የጥብቅ ቡድን ተማሪዎች ግን በተለምዶአዊ ወይም በመደበኛ የማስተማሪያ ዘዴ ንግግርን ተምረዋል፡፡ ለክፍል ደረጃው በሳምንት አንድ ክፍለ ጊዜ የተመደበለት ሲሆን የዚህ ጥናት አቅራቢ በሁለቱ ክፍሎች ተመሳሳይ የትምህርት ይዘት እንዲቀርብላቸው አድርጓል፡፡

ለሙከራዊ ቡድኑ ማሰተማሪያ የተለያዩ ክርክራዊ ርእሶችን እንደ ትምህርቱ (ክርክሩ) ይዘት ተማሪዎቹ እንዲገነዘቡ ተደርገው በተግባር ላይ ውሏል፡፡ አብዛኛው የክርክር ዓይነት የቡድን ሥራ የሚጠይቅ በመሆኑ አላማውን በተመለከተ ለተማሪዎች በቂ መረጃ ተሠጥቷል፡፡ ሞዴል ክርክሮችን በማሳየት በቀጣይ በራሳቸው ልምምድ እንዲያደርጉ መመሪያ ተሰጥቷቸዋል፡፡ በዚህ መልኩ የትምህርቱን አላማ ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችሉ የክርክር ዓይነቶች እየተመረጡ ተግባራዊ ሆነዋል፡፡ይህም በአባሪ አምስት ላይ ተመልክቷል፡፡

## 3.3 የመረጃ መሰብሰቢያ መሰሪያዎች

የጥናቱን ዋና አላማ ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት የተመረጡት የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎች ለንግግር ስልታዊ አተገባበር የንግግር ክሂልን ውጤታማነትን የሚያሳይ ምልከታ (observation ) እና የተጠኚዎችን የትምህርት ውጤት ሊያስገኝ የሚችል ቃላዊ የንግግር ፈተና (test) ናቸው፡፡

### 3.3.1 ፈተና (Test)

ፈተና በቀላል መንገድ የሰዎችን ችሎታ፣ እውቀት እና የስራ አፈፃፀም በአንድ በተሠጠው ነገር ላይ መመዘን የሚችል ነው በማለት Brown (2004:3) ይገልፃሉ፡፡

በዚህ ጥናት ለሙከራ የተመረጡትን ተማሪዎች የንግግር ክሂል አቅማቸውን ለማግኘት ያገለግላል ተብሎ በመረጃ መሰበሰቢያ መሣሪያነት እንዲውል ፈተና ተመርጧል፡፡በዚሁ መሰረት ፈተና የዚህ ጥናት ዋነኛ የመረጃ መሰብሰቢያ ሆኖ አገልግሏል፡፡

በክፍል አንድ እንደተጠቀሰው፣ የጥናቱ ዓቢይ ዓላማ በሙከራዊ ቡድኑ እና በጥብቅ ቡድኑ የሚታየውን የውጤት ተቀራራቢነት እና ልዩነት በመፈተሽ ሙከራዊ ቡድኑን ውጤታማ መሆን አለመሆኑን መለየት እንደመሆኑ፣ አጥኚው ተማሪዎች የራሳቸውን የህይወት ታሪክ እንዲናገሩ እና እንዲገልጹ በማድረግ ቃላዊ የመናገር ክሂል ፈተና መመዘኛ  የሆኑትን ቃላት ፣ ስዋስው፣ ንበትና ፍሰት መሰረት በማድረግ የተማሪዎች የቅድመ ችሎታ መለኪያ ፈተና (pre-test) እና የተማሪዎች የድህረ ደረጃ ችሎታ መለኪያ ፈተናዎች (post-test) በዋናነት የሚያገለግሉ የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያ ሆነዋል፡፡እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት ነጥቦች ቃላት ፣ሰዋስው ፣ ንበትና ፍሰት የሚባሉት አራቱ Brown (2004;173) ያስቀመጣቸው ቃላዊ የመናገር ክሂል ፈተና መመዘኛዎች ናቸው፡፡በዚሁ መሰረት እያንዳንዳቸው 25% ነጥብን ይይዛሉ፡፡ይህ ማለት 4x25=100 ማለት ነው፡፡ በዚህ መሠረት በተሰጠው አመላካች ትልቁ ነጥብ መቶ ፐርሰንት ሲሆን በአጠቃላይ የግምገማው ውጤት በአራቱ ቃላዊ የንግግር መመዘኛ መስፈርት በገጽ 18 በክለሳ ድርሳናት ጽሑፍ ውስጥ ላይ ተመስርቶ ቃላዊ የንግግር ምዘና ተሰጥቷል ይህም በአባሪ ሦስት ተጠቅሷል፡፡

የቅድመ ችሎታ መለኪያ ፈተና አንድ ሰው ወደ ስልጠና ወይም ወደ ትምህርት ከመምጣቱ በፊት የሚኖረውን የብቃት ደረጃ ለመለካት የሚያስችል የፈተና ዓይነት ነው፡፡ ዓለም (1997፡70)፡፡በመሆኑም በዚህ ጥናት የቅድመ ችሎታ ፈተና የተሰጠው በሙከራዊ ቡድኑና በጥብቅ ቡድኑ መካከል ያለውን የውጤት ተቀራራቢነት ወይም ልዩነት ለማወቅ የሚያስችል መረጃ መሰብሰያ ሆኖ አገልግሏል፡፡የቅድመ ፈተና ውጤቱ ተማሪዎች በትምህርቱ ካለፉ በኋላ የሚያስመዘግቡት ውጤት ማነጻጸሪያ ሆኖ አገልግሏል፡፡በሌላ በኩል ድህረ የችሎታ መለኪያ ፈተና ተማሪዎች የተወሰነ ትምህርት ከተማሩ በኋላ የሚቀርብ ፈተና ሲሆን ተማሪዎች ከትምህርቱ በኋላ ፈተናውን ወስደው ያሳዩትን ብቃት መዝኗል፡፡በዚህ ጥናት ተማሪዎች በተለያዩ የክርክር ማስተማሪያ ዘዴ ተምረው የችሎታ መለኪያ ፈተና ወስደዋል፡፡ በዚሁ መሠረት በሙከራዊ ቡድኑና በጥብቅ ቡድኑ መካከል ያለውን ውጤት ተቀራራቢነትና ልዩነት ለማወቅ የሚያስችል መረጃ ተሰብስቧል፡፡

የጥናቱ አቅራቢ በደረጃው ያሉ የመማሪያ መጽሐፍትን የመልምጃ አቀራረብንና በተዛማጅ ጽሑፍ የተጠቀሱ የመልመጃ ዓይነቶችን መሠረት በማድረግ ቃላዊ የንግግር ክሂል መመዘኛ ፈተናዎችን በተገቢ ሁኔታ እንዲዘጋጁ ጥረት አድርጓል፡፡የተዘጋጁት ፈተናዎች በትምህርት ቤቱ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍልና በትምህርት ቤቱ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ተገምግሞ በአማካሪ ከጸደቀ በኋላ ተግባራዊ ሆኗል፡፡ጥያቄዎቹ ሲዘጋጁ ተማሪዎቹን ይመጥናቸዋል ወይም መግለጽ ይችላሉ ተብሎ የታመነበት ነው፡፡በፈተናው የሁለቱም ቡድኖች ተመሳሳይ ጊዜና ግብዓት ተሰጥቶአቸዋል፡፡ በመቀጠልም ፈተናዎቹ ለተማሪዎች ቀርበው ተግባራዊ ከሆኑ በኋላ በአጥኝውና በትምህርት ቤቱ ተባባሪ መምህራን በቀረበው መመሪያ መሠረት ታርሟል፡፡

ተማሪዎች በሁለት ቡድን የተከፈሉ ሲሆን ስማቸው በየክፍላቸው ለየብቻ ተመዝግቧል፡፡ በንግግር ክሂል ላይ የተዘጋጁ በሌሎች ሦስት የቋንቋ መምህራን ትክክለኛነቱ የተረጋገጠ ቅድመ ፈተና (pre test) ቀርቦላቸዋል፡፡ያገኙትም ነጥብ ተመዘገቦላቸዋል ይህም አባሪ ዘጠኝ ላይ ይገኛል፡፡ በመቀጠልም የሙከራ ቡድኑ ትምህርቱን በክርክራዊ ስልት አተገባበር ንግግርን ተምረዋል፡፡ይህም በአባሪ አምስት ላይ ተመልክቷል፡፡ ለጥብቅ ቡድኑም በመደበኛው ወይም በተለምዶአዊው የትምህርት አሰጣጥ ንግግርን ተምረዋል፡፡

ከዚያ ድህረ ፈተና (post test) ለሁለቱም ቡድኖች ቃላዊ የንግግር ክሂል መመዘኛ ፈተና ተሰጥቷቸዋል፡፡ በመጨረሻም በፈተናው የተገኘው ውጤት በአባሪ 12 ላይ ተዘርዝሯል፡፡

### 3.3.2 ምልከታ

Hopskills. (1993:16) ስለ ክፍል ምልከታ በተመለከተ እንዲህ ሲሉ ያስቀምጣሉ፡-
አጥኚው የምልከታን ቼክ ሊስት በማዘጋጀት በቼክ ሊስቱ መሠረት ወይም አመልካችነት የተማሪዎችን የክፍል ውስጥ ክንውን ያያል ይላሉ፡፡ የተማሪዎችን መረዳትና ግንዛቤ ካስቀመጠው ቼክ ሊስት መመዘኛ በመጠቀም ተማሪዎች ያሉበትን ደረጃ በተገኘው የቼክ ሊስት አማካይ ውጤት መዝኗል፡፡ በዚህም መሰረት የተማሪዎችን እንቅስቃሴ፣ተሳትፎ ወይም ትግበራ በመማርና ማስተማር ሂደት ውስጥ የነበራቸውን ሁናቴና አመለካከት አይቷል፡፡

ምልከታ መረጃን በሱፐርቪዥን መልክ ለማግኘት ከምንጠቀምባቸው ዘዴዎች አንዱ ነው፡፡ በመሆኑም አጥኚው መምህር በተባባሪ መምህራን ሲረዳ ቆይቷል፡፡ በተባባሪነት በክፍል ውስጥ የሚገቡት ተባባሪ የቋንቋ መምህራን ምልከታውን ከማድረጋቸው በፊት በአጥኝው ስለ ምልከታው ቼክ ሊስት አሞላልና ዝርዝር ሁኔታውን በተመለከተ ስልጠና ተሰጥቷል፡፡በመቀጠልም ተባባሪ መምህራኑ በምልከታው የተዘጋጀ ቼክ ሊስት ይዘው በመግባት የተማሪዎችን ስሜት፣ አመለካከትና ቋንቋ መማር ማስተማር ሂደት በክፍለ ጊዜው የሚከናውኑትን ድርጊት እየመዘገቡ ሙያዊ ማስታወሻ በያዙት ቼክ ሊስት መሰረት ሞልተዋል፡፡በክፍል ውሰጥ የታዩትን የክፍል ውስጥ የመማር ማስተማር ሂደት በምልከታ ውጤታቸው ገልጸውታል፡፡ይህን የምልከታ ቼክ ሊስት አጥኝው ከ Richa Rubiati (2010) “በዋሊሶንጎ ግዛት በታርቢያህ ሶማራንግ ተቋም (IAIN Walisongo State Institute For Islamic Stadies, Semarang) “ Nunan, (1993) መሰረት በማድረግ ባደረገው የክርክር ውጤታማነት ፍተሻ ጥናት ላይ ከተጠቀመው የምልከታ ቅፅ በቀጥታ በመውሰድ እና ከሀገራችን የትምህርት ይዘት ጋር በማጣጣም ለጥናቱ በምልከታ ለሚገኙ መረጃ መሰብሰቢያነት ጥቅም ላይ አውሎታል፡፡

**ሠንጠረዥ 3.1** የምልከታ ቼክ ሊስት

| ተ.ቁ | የተማሪዎች የክፍል ውስጥ አተገባበር | የነጥብ አሰጣጥ | | | | | ጠቅላላ ድምር |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 | |
| 1 | መምህሩ በክፍል ውስጥ ለሚያደርገው ገለጻ ተማሪዎች ትኩረት ይስጣሉ፡፡ | | | | | | |
| 2 | በክፍል ውስጥ በተደራጀው የቡድን ሂደት ተማሪዎች ራሳቸውን መምራት ይችላሉ፡፡ | | | | | | |
| 3 | ተማሪዎች በተሰጣቸው ነገር ላይ በጥሩ ቅልጥፍና የመሳታፍ ፍላጎት አላቸው፡፡ | | | | | | |
| 4 | ተማሪዎች ለክርክሩ አተገባበር ጥሩ ሚና አላቸው፡፡ | | | | | | |
| 5 | ተማሪዎች የተሰጣቸውን ክርክር ለማዳበር የተወሰኑ ማስታወሻዎችን ይይዛሉ፡፡ | | | | | | |
| 6 | ተማሪዎች በተገቢው ሁኔታ የሚያደርጉትን ክርክር በሚሰማ ድምጽ የመግለጽ አቅም አላቸው፡፡ | | | | | | |
| 7 | ተማሪዎች ለክርክሩ ተገቢ የሆነ ስተያየትበመስጠት ቅልጥፍናቸውን ያሳያሉ፡፡ | | | | | | |
| 8 | ተማሪዎች በክርክሩ ውስጥ የተለየ ምላሽ እና አስትያየት በመስጠት ይሳተፋሉ፡፡ | | | | | | |
| | ጠቅላላ ድምር | | | | | | |

1. _< 54 % = በጣም ዝቅተኛ
2. 55_59 % = ዝቅተኛ
3. 60-75 % = በቂ
4. 76-85 % = በጣም ጥሩ
5. 86-100 % = እጅግ በጣም ጥሩ

ከላይ በተጠቀሰው የምልከታ ውጤት መመዘኛ መሰረት ከምልከታ የተገኘው ውጤት ተማሪዎች በመማር ሂደት ውስጥ ያላቸውን ባህሪ መሰረት ያደረገ እንዲሁም በክፍል ውስጥ የክርክር ትምህርት ሲሰጥ ያላቸውን እንቅስቃሴና አተገባበራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

በዚህ ጥናት አጥኚው አማካይ ቀመር (mean formula) ተጠቅሟል፡፡ይህም የተማሪዎችን አማካይ ውጤት በማግኘት የተማሪዎችን በክፍል ውስጥ በክርክራዊ ስልት ንግግርን ሲማሩ

የነበራቸውን ጠቅላላ ሁኔታ ተሳትፎና አመለካከት መሻሻሉን ለማረጋገጥ እንዲሁም ያሉበትን ደረጃ ለመለየት አጥኝው ተጠቅሟል፡፡

ከዚህ የምልከታ ቼክ ሊስት ውጤት በመነሳት ተማሪዎች በመጀመሪያ የነበራቸውን የክፍል ውስጥ ጠቅላላ አመለካከትና እንቅስቃሴ እንዲሁም የክፍል ውስጥ ነባራዊ ሁኔታን፣ ትምህርቱ ከተጀመረና እየተማሩ ያሉበትን ደረጃ የሚገልጸውን ሁለተኛ የምልከታ ቼክ ሊስት ውጤት በማቀናጀት ተነጻጽረው ልዩነታቸው ተቀምጧል፡፡

## 3.4 የመረጃ መተንተኛ ዘዴ

የጥናቱን መሠረታዊ ጥያቄዎች ለመመለስ ከናሙና ምርጫና ከመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ቀጥሎ ተገቢ የሆነ የመረጃ ትንተና ለጥናቱ ውጤት እጅግ ወሳኝ ነው፡፡ በመሆኑም በዚህ ጥናት በፈተና እና በምልከታ የተሰበሰቡት መረጃዎች በሚከተሉት የመረጃ መተንተኛ ስልቶች አማካኝነት ተተንትነዋል፡፡

1.አማካይ ውጤት

በአማካይ ውጤት ቀመራዊ አህዝ በምልከታና በፈተና የተገኙት መረጃዎች ተተንትነውበታል፡፡ በትንተናው ከሁለቱ ዙር የተገኘው የክፍል ውስጥ ምልከታ አማካይ ውጤት (mean score) በንጽጽር ቀርቧል፡፡ እንደገናም በቃላዊ ፈተና የቀረቡት የቃላት፣ የስዋስው፣ የንብት እና የፍሰት የመናገር ክሂል ምዘና ውጤቶች (scores) ለየብቻ ራሳቸውን ችልው ከሙከራዊ ቡድኑ እና ጥብቅ ቡድኑ አንጻር በአማካይ ውጤት ንጽጽር ቀርበዋል፡፡

2.ቲ -ቴስት

በመጀመሪያ በሙከራዊ ቡድኑ እና በጥብቅ ቡድኑ የተመዘገቡ የቅድመ ፈተና ውጤቶች አማካይ ውጤት በንጽጽር ቀርቧል፡፡አማካይ ውጤት በሁለቱ ቡድኖቸ መካከል ያለውን የውጤት ተቀራራቢነት እና ልዩነት በተወሰነ ደረጃ ያሳያል፡፡ነገር ግን በሁለቱ ቡድኖች መካከል ያለውን የውጤት ልዩነት ወይም የጉልህነት ድረጃ ወይም መበላለጥ እምብዛም አያሳይም ፡፡በመሆኑም በሁለቱ ቡድኖች ውጤት መካከል ያለው የጉልህነት ደረጃ (Level of significance) የጎላ መሆን አለመሆኑን ለመለየት ወይም ለማረጋጥ የሚቻለው ከቲ-ቴስት አይነቶች አንዱ በሆነው በነጻ ናሙና ቲ-ቴስት ቀመር ነው፡፡

ያለው(1998፡289-291) በመሆኑም ሁለቱ ቡድኖች በቅድመ ፈተና ምዘና ያስመስመዘግቡት የጎላ የውጤት ልዩነት ስለልታየበት (ተመሳሳይ ወይም ተቀራራቢ ስልሆነ) ይህም ማለት የሙከራ ቡድኑ እና የጥብቅ ቡድኑ በቀረበላቸው ቃላዊ ፈተና ያገኙት አማካይ ውጤት የተቀራረበና በአንድ አይነት ደረጃ ውስጥ የሉ መሆናቸውን ያሳያል፡፡ስለዚህ በቀጣይ በድህረ ፈተና ለሚያስመዘግቡት ውጤት መነጻጸሪያ ሆኗል፡፡ ይህም በአብሪ 10 ላይ ተመልክቷል፡፡

በተመሳሳይ ሁኔታ ሙከራዊ ቡድኑ እና ጥብቅ ቡድኑ በድህረ ፈተና ምዘና የሚያስመዘግቡት ውጤት በስታቲክሳዊ ቀመር አማካይ ውጤት በንጽጽር ቀርቧል፡፡በመቀጠልም በሁለቱ ቡድኖች መካከል ያለው የጉልህነት ደረጃ የጎላ መሆን አለመሆን በቲ-ቴስት ቀመር ተለይቷል፡፡የቲ-ዋጋ (T-value) ከቲ-ሰንጠረዥ ዋጋ (T-critical value) እና ከቲ-የነጻነት ደረጃ (T-level of freedom) ጋር በማወዳደር የጉልህነት ደረጃውን ወስኗል፡፡በቀመሩ ስሌት መሰረት የሚገኘው የቲ-ዋጋ ከቲ-የሠንጠረዥ ዋጋ ከበለጠ ልዩነቱ የጎላ ነው ማለት ነው፡፡

በመጨረሻም የሁለቱ ቡድኖች በመናገር ክሂል ቅድመ ፈተና (pre-test) እና ድህረ ፈተና (post test) የተገኘውን የጉልህነት ደረጃ በማነጻጸር በክርክራዊ ስልት አተገባበር ዘዴ ማስተማር ለተማሪዎች ውጤታማነት ያለውን ሚና ለመረዳት ተችሏል፡፡ ይህም አባሪ 14 ላይ ተመልክቷል፡፡

# ምዕራፍ አራት

## 4.1 የመረጃ ትንተና እና ውጤት ገለጻ

ጥናቱ ዓላማ አድርጎ የተነሳው በኦሮሚያ ክልል በጅማ ዞን በሊሙ ኮሳ ወረዳ በሊሙ ገነት ከተማ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች የመናገር ክሂል በክርክራዊ ስልት የማስተማር ዘዴ ውጤታማነትን ፍተሻ ለማየት ነው ፡፡ ስለሆነም በክፍል ውስጥ ምልከታና በፈተና (ቅድመ ችሎታ ፈተና እና ድህረ ችሎታ ፈተና ) የተሰበሰቡ መረጃዎችን በቅደም ተከተል አጥኝው ተንትኗል፡፡በዚሁ መሰረት ጥናቱ በጥብቅ ቡድኑና በሙከራ ቡድኑ መካከል ያለውን ተቀራራቢነትና ልዩነት በንጽጽር ገልጿል፡፡

### 4.1.1 የውጤት ትንተና

ለጥናቱ የተሰበሰቡ መረጃዎች የተተነተኑት ከተመጋጋቢነታቸው አንጻር ስለሆነ መጀመሪያ የክፍል ውስጥ ምልከታ ውጤት ቀጥሎ የፈተናው (የቅድመ ችሎታ ፈተና ውጤትና የድህረ ችሎታ ፈተና ውጤት ) በጥብቅ ቡድኑ እና በሙከራ ቡድኑ መካከል የታየውን ልዩነትና መቀራረብ ተተንትነዋል፡፡

### 4.1.2 የክፍል ውስጥ ምልከታ መረጃዎች ትንተና

የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የመናገር ክሂል በክርክራዊ ስልት ትምህርቱ ከመሰጠቱ በፊት በናሙናነት የተመረጡት ተማሪዎች በመማር ማስተማር ሂደት ውስጥ ያላቸውን የክፍል ውስጥ እንቅስቃሴ ፣ ተሳትፎ ፣ አመለካከት እና ክንውን በተባባሪነት በክፍል ውስጥ ለምልከታ የገቡት ሁለት የቋንቋ መምህራን ለምልከታው የተዘጋጀ ቼክ ሊስት ይዘው በመግባት የተማሪዎችን ስሜት ፣ የክፍል ውስጥ እንቅስቋሴ ፣ አመለካከትና በቋንቋው መማር ማስትማር ሂድት በክፍለ ጊዜው የሚከናወኑትን ድርጊት እየመዘገቡ ሙያዊ ማስታወሻ በመያዝ በተሰጠው አመላካች መሰረት ነጥብ በመስጠት በያዙት ቼክ ሊስት ላይ ሞልተዋል፡፡በክፍል ውስጥ የነበረውን ነባራዊ ሁኔታ የታዩትን የክፍል ውስጥ የመማር ማስተማር ሂድት በምልከታ ውጤታቸው ገልጸውታል፡፡

አጥኚው ይህን የመጀመሪያ ዙር በሁለት ተባባሪ መምህር የተሞላውን የምልከታ ውጤት በአማካይ ነጥብ (mean score) በመውሰድና በመመዘን ተማሪዎች ያሉብትን ጠቅላላ ሁኔታ ከተሰጣቸው አማካይ ነጥብ አኳያ አብራርቷል፡፡

**ሠንጥረዥ 4.1 የመጀመሪያ ዙር የምልከታ ውጤት**

| ተ.ቁ | የተማሪዎች የክፍል ውስጥ አተገባበር | የነጥብ አሰጣጥ | | | | | ጠቅላላ ድምር |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 | |
| 1 | መምህሩ በክፍል ውስጥ ለሚያደርገው ገለጻ ተማሪዎች ትኩረት ይሰጣሉ:: | | X | | | | 4 |
| 2 | በክፍል ውስጥ በተደራጀው የቡድን ሂደት ተማሪዎች ራሳቸውን መምራት ይችላሉ:: | | | X | | | 3 |
| 3 | ተማሪዎች በተሰጣቸው ነገር ላይ በጥሩ ቅልጥፍና የመሳታፍ ፍላጎት አላቸው:: | | | X | | | 3 |
| 4 | ተማሪዎች ለክርክሩ አተገባበር ጥሩ ሚና አላቸው:: | | | X | | | 3 |
| 5 | ተማሪዎች የተሰጣቸውን ክርክር ለማዳበር የተወሰኑ ማስታወሻዎችን ይይዛሉ:: | | X | | | | 4 |
| 6 | ተማሪዎች በተገቢው ሁኔታ የሚያደርጉትን ክርክር በሚሰማ ድምጽ የመግለጽ አቅም አላቸው:: | | | X | | | 3 |
| 7 | ተማሪዎች ለክርክሩ ተገቢ የሆነ አስተያየት በመስጠት ቅልጥፍናቸውን ያሳያሉ:: | | | X | | | 3 |
| 8 | ተማሪዎች በክርክሩ ውስጥ የተለየ ምላሽ እና አስተያየት በመስጠት ይሳተፋሉ:: | | | X | | | 3 |
| | **ጠቅላላ ድምር** | | | | | | 26 |

$$\text{አማካይ} = \frac{\text{ጠቅላላ ውጤት}}{\qquad} \times 100$$

$$\text{አማካይ} = \frac{26}{40} \times 100$$

አማካይ = 65

በሠንጠረዥ 4.1 በታየው የምልከታ ቼክ ሊስት አማካይ ውጤት መሰረት በመጀመሪያ ዙር ምልከታ ለሙከራ ቡድን በተመረጡት ተማሪዎች ላይ የተደረገ የምልከታ ውጤት ነው፡፡ይህም የምልከታ ቼክ ሊስት የአጥኚው ተባባሪ መምህራኖች ተማሪዎች ትምህርቱን ሳይጀምሩ አጥኚው በክፍል ውስጥ የተማሪዎችን ስም በመጥራት የመጡና የቀሩ ተማሪዎችን በመለየትና በቀጣይ ለሚያደርጉት የክፍል ውስጥ የመማር መስተማር ሂደትና የክፍል ውስጥ አተገባበርና ተሳትፎ ተማሪዎችን በአዎንታዊ ቡድን እና በአሉታዊ ቡድን በመከፋፈልና በመመደብ እያንዳንዱ ተማሪ በተመደበበት ቡድን ውስጥ በተነቃቃ ሁኔታ ጥሩ ተሳትፎ በማድረግ በተመደበበት ቡድን ውስጥ ተንቀሳቅሶ ለራሱም ለቡድኑም ውጤት ማስመዝገብ እንዳለበት ግንዛቤ እንዲያገኙ ገለጻ ሰጥቷል፡፡

በዚህ ሂደት ውስጥ የአጥኚው ተባባሪ መምህራን ይዘው የገቡትን የምልከታ ቼክ ሊስት መሰረት በማድረግ የተማሪዎችን የክፍል ውስጥ እንቅስቃሴ፣ ተሳትፎና አመለካከት በማየት ሙያዊ ማስታወሻ በተቀመጠው ማመላከቻ ላይ በመመርኮዝ ነጥብ ሰጥተዋል፡፡አጥኚውም ሁለቱ ተባባሪ መምህራን በምልከታው ቼክ ሊስት አመላካች መሰረት የሞሉትን አማካይ በመውሰድ እና በማጠጋጋት የምልከታ ቅጹን ሞልቷል፡፡በዚሁ መሰረት የተሰጠው ነጥብ በአማካይ ቀመር (mean formula) ተሰልቶ 65% መጥቷል፡፡ይህ ማለት በገጽ 34 በተቀመጠው የምልከታ አመላካች መመዘኛ መሰረት ከ60% - 75 % ድረስ ያለው አማካይ ነጥብ በቂ የሚለውን ደረጃ ይመዝናል፡፡በዚሁ መሰረት በመጀመሪያው ዙር የምልከታ ውጤት ተማሪዎች በቂ የሚለውን መመዘኛ ነጥብ አግኝተዋል ማለት ነው፡፡ ከዚህም በመቀጠል ሁለተኛውን ዙር የምልከታ ውጤት በሚከተለው ሰንጠረዥ ተመልክቷል፡፡

**ሠንጠረዥ 4.2 ሁለተኛ ዙር የምልከታ ውጤት**

| ተ.ቁ | የተማሪዎች የክፍል ውስጥ አተገባበር | የነጥብ አሰጣጥ | | | | | ጠቅላላ ድምር |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 | |
| 1 | መምህሩ በክፍል ውስጥ ለሚያደርገው ገለጻ ተማሪዎች ትኩረት ይሰጣሉ፡፡ | X | | | | | 5 |
